# የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት እንደገና ተሻሽሎ የወጣ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር፳፰/፪፻፲

## የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ታህሳስ ፪፻፲ □/ም

ሀዃሳ

## ማ□ጐ□


| አንቀጽ | | ርክስ | ቁ□ |
|---|---|---|---|
| **□ኣል** | **፩** | **□ቅላላ** | **1** |
| | ፩ | አጭር ርዕስ | 1 |
| | ፪ | ትርጓሜ | 1 |
| | ፫ | የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን | 2 |
| | ፬ | መርሆዎች | 2 |
| **□ኣል** | **፪** | **ተግባርና ኃላፊነት** | **3** |
| | ፭ | የመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት | 3 |
| | ፮ | □ፅዴ ፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት | 7 |
| | ፯ | የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት | 11 |
| **□ኣል** | **፫** | **□ፅዴ ክቅት** | **12** |
| | ፰ | የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት | 12 |
| | ፱ | የግዥ ፍላጐትን መለየት ማሰባሰብና ማደራጀት | 13 |
| | ፲ | □ፅዴ □ጸ መምረዓ | 15 |
| | ፲፩ | የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን | 16 |
| | ፲፪ | የግዥ ዕቅድ ይዘት | 16 |
| | ፲፫ | የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ | 17 |
| | ፲፬ | □መታዊ የግዥ ዕቅድን ይፋ ማድረግ | 18 |
| **□ኣል** | **፬** | **የግዥ ዘዴዎች አፈጻጸማቸው** | **18** |
| | ፲፭ | የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች | 18 |
| | ፲፮ | □ብሄራዊ ዕል□ ፊ ረታ ግዥ አፈጻጸም | 19 |
| **□ኣል** | **፭** | **የዓለም አቀፍ ግዥ አፈጻጸም** | **64** |
| | ፲፯ | ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ | 64 |
| | ፲፰ | ሌሎች አለም አቀፍ ግዥዎች | 66 |
| | ፲፱ | በሁለት ደረጃ ጨረታ □ሚ□□ም ዕዴ | 66 |
| | ፳ | የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ | 68 |
| | ፳፩ | በመ□ቴ□ሪጸ ሀሳብ መ□□ቂጸ □ሚ□ናም ዕዴ | 70 |
| | ፳፪ | የፍላጐት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ | 76 |
| | ፳፫ | የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም | 77 |
| | ፳፬ | በአካባቢ ማስታ□ቂጸ በመለ□አ □ሚ□ናም ዕዴ | 80 |
| | ፳፭ | ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ | 82 |
| **□ኣል** | **፮** | **ል□ ዕዴ** | **88** |
| | ፳፮ | በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃና አገልግሎቶች ልዩ ግዥ | 88 |
| **□ኣል** | **፯** | **የውል አስተዳደር** | **94** |
| | ፳፯ | ውልን ተፈጻሚ ማድረግ | 94 |
| | ፳፰ | የውል አፈጻጸምን መከታተል | 96 |
| | ፳፱ | ውል ማጠናቀቅ | 97 |
| **□ኣል** | **፰** | **ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** | **98** |

፴ መ□በኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር ................ 98
፴፩ የግዥ ሠነዶች ........................................................................ 98
፴፪ የአቅራቢዎች ምዝገባ እና በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ................................................................. 100

□ አል ፱ **የመንግስት ግዥ ሥነ ምግባር ............................................ 102**

፴፫ ከግዥ ባለሙያ የሚጠበቅ ሙያዊ ሥነ ምፅባር ........................ 102
፴፬ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ ምግባር .............................. 105

□ አል ፲ **በመንግስት ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪና ውሣኔ ሰጪ ቦርድ ........................................................................ 105**

፴፭ የቦርድ አባላት ስያሜና የሥራ ዘመን ........................................... 105
፴፮ □ቦርት ስብሰባ ........................................................................ 106
፴፯ ከቦርድ አባልነት መልቀቅ ............................................................ 106
፴፰ የቦርድ አባልነት መቋረጥ.............................................................. 106
፴፱ የጥቅም ግጭትን ስለመግለጽ ........................................................ 107
፵ የቦርዱ ሥልጣን.......................................................................... 107
፵፩ □ቦርዐ ተፅባር ........................................................................ 108

□ አል ፲፩ **ለመንግስት መ/ቤት የበላይ □ኃላፊ ወይም ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ □ሚታይበት ሥርዓት ........................... 109**

፵፪ □ክፋ ተ□ቱቴሪ □ጁም ተጫራች አቤቱታ የማቅረብ መብት....... 109
፵፫ አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ................................ 109
፵፬ ለመንግስት መ/ቤት የበላይ □ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት.......................................................................... 110
፵፭ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻላቸው 111
፵፮ አቤቱታ ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብበትና የሚጣራበት ሥርዓት........112

□ አል ፲፪ **ለኤጀንሲው የሚቀርብ □ዓኛተኛነት ሪፖርት የሚታይበት ሥርዓት 113**

፵፯ □ዓኛተኛነት ሪፖርት የሚቀርብበትና የሚጣራበት ሥርዓት ....... 113
፵፰ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ............................................................ 116
፵፱ አቤቱታን በፍርድ ቤት ሰለማየት .................................................. 116

□ አል ፲፫ **□ዙሻሩ መመሪያዎች እና ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ ...............117**

፶ □ዙሻሩ መመሪያዎች ..................................................................117
፶፩ መመሪያው የሚፀናበት ቀን .......................................................... 118

# አባሪዎች

አባሪ ቁዓ ር ፩ □መታዊ □ፅዴ ክቅት የሚዘጋጅበት ቅ□

አባሪ ቁዓ ር ፪ በክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ስለተከናወኑ ግዥዎች ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

አባሪ ቁዓ ር ፫ ፊ ረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ

አባሪ ቁጥር ፬ በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እና ለሕንጻ ግንባታ □ሚገዙት
ማሽነሪዎች ዝርዝር

አባሪ ቁጥር ፭ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ ዋና ዋና ኃላፊነቶች

አባሪ ቁጥር ፮ በተጫራቾች የሚሞላ □ፊ ረታ ማስከበሪያ ዋስትና

አባሪ ቁጥር ፯ በግንባታ ሥራዎች ግዥ ላይ የሚጠየቀው የሥራ ልምድና የብቃት መስፈርቶች

## መግቢያ

የክልሉ መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልሉ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 146/2004 አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከታህሳስ 2005 ዓ/ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለውን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2005ን አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ለክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ማሰራጨቱ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው መ/ቤቶች የሚፈጽሙትን ግዥ በተሻለ ሁኔታ ሊያስፈጽም በሚያስችል መልኩ በየጊዜው እየተፈተሸ መሻሻል የሚገባው በመሆኑ ቢሮው ከተለያዩ ባለድርሻ አካለት በቀረበ የማሻሻያ ሀሳብ መነሻ ጥናት ካደረገ እና በጥናቱ በተገኙ የማሻሻያ ሀሳቦች ዙሪያ የተለያዩ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እንዲመክሩበት ካተደረገ በኋላ ነጥረው የወጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን እንዲሁም መመሪያውን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በአዲስ መልክ አዘጋጅቷል፡፡ መመሪያውን ለማሻሻል ምክንያት የሆኑ አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ሁኔታዎች፡-

ሀ. ለግዥ ዘዴዎች በመመሪያው የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ አሁን ያለውን የገንዘብ የመግዛት አቅም ባገናዘበ መልኩ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

ለ. ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችን በአግባቡ ሊያሰሩ ያልቻሉ የመመሪያው የአሰራር ሥርዓቶችን ፈትሾ በተሻለ ሁኔታ ሊያሰራ በሚችል መልኩ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሐ. በተለያዩ የመ/ቤቶች አደረጃጀትና የመዋቅር ለውጦች ምክንያት የተለወጡ ስያሜዎች ወይም ተግባርና ኃላፊነቶች ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

መ. በግንባታ ዘርፍ ግዥዎች አፈፃፀም ዙሪያ ለኪራይ ሰብሳቢነት በር የሚከፍቱ የአሰራር ሥርዓቶች ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሠ. በመንግስት ግዥ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለያዩ መድረኮች ያቀርቡ ከነበረው ጥያቄዎች ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገቡትን ለይቶ

ስለሆነም የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች መመሪያው ፀድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የሚፈጽሙትን ማንኛውም ግዥ በዚህ መመሪያ የአሰራር ሥርዓቶች መሠረት መፈፀም የሚገባቸው መሆኑን እናሳስባለን ፡፡

# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፪ሺ፩ አንቀጽ ፸፯/፪ እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፻፳፩/፪፻፻፳ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደገና አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

## ክፍል ፩

## ጠ ቅ ላ ላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ጁህ መመሪጸ '' የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት እንደገና ተሻሽሎ የወጣ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁዓ ር ፳፳/፪፻፻፲ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ  አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ጸሉ ቃላትና ሐረጎች በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፪፻፻፩ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪጸ □ስዓ :-

ሀ/ ''የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ "ማለት ዕቃው፣ አገልግሎቱ፣ የግንባታ ሥራው ወይም የምክር አገልግሎቱ ሊያሟላ  የሚገባውን ጥራት፣ ዓይነትና ደረጃ የሚገልጽ ሰነድ ነው፡፡

ለ/ "አዋጅ" ማለት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፻፵፯/፪፻፻፩ ማለት ነው፡፡

ሐ/ "ጨረታ" ማለት የጨረታ ማስታወቂያው ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚገልጽ ነው።

መ/ "የግዥ ዳይሬክቶሬት " ማለት የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች እንደስራ ባሕሪያቸው የሚያደራጁት ሆኖ በመ/ቤቱ የሚፈፀሙ ግዥዎችን እና በሽያጭ የሚወገዱ ንብረቶችን ሽያጭ እንዲያከናውን ኃላፊነት የሚሰጡት ወይም በግ/ፋ/ን/አስ/ዳይሬክቶሬት ውስጥ የግዥ እና የንብረት ሽያጭ ተግባርን እንዲፈጽም ኃላፊነት የሚሰጡት አካል ማለት ነው።

ሠ/ "መደበኛ የጨረታ ሠነድ " ማለት የመንግስት መ/ቤቶች አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሠነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ የሚረዳ በክልሉ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተዘጋጀ ሠነድ ነው።

ረ/ "ጠቅላላ ዋጋ" ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት በመንግስት መ/ቤቱ ለሚፈፀም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው።

ሰ/ "የጋራ ግዥ ፈፃሚና ንብረት ማስወገድ ዳይሬክቶሬት" ማለት በክልሉ መንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ግዥ እንዲፈጽም እና የክልል ሴክተር መ/ቤቶችና ክልላዊ ተቋማት በሽያጭ እንዲወገዱ የወሰኗቸውን ተሽከርካሪና ማሽነሪዎች በሽያጭ እንዲያስወግድ በክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውስጥ የተደራጀ ዳይሬክቶሬት ማለት ነው።

## ፫. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንበት በማናቸውም የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፬. መርሆዎች

ማናቸውም ግዥን ለማስፈፀም የተሰጠ ሥልጣን እና የግዥ አፈፃፀም ተግባር የሚከተሉትን መርሆዎች ከግብ ማድረስ ይኖርበታል።

ሀ/ በግዥ አፈፃፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣

ለ/ በአዋጁ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ አለመከልከልን ወይም አድልዎ አለማድረግን፣

ሐ/ የመንግስት ግዥ አፈፃፀምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት መደገፍ፣

መ/ ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ ማድረግ፣

ሠ/ ከግዥ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሳኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥ፣

ረ/ በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሰረት የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፉ የሀገር ውስጥ አምራቾችን፣ ኩባንያዎችን እና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማበረታታት።

## ክፍል ፪

## ተግባርና ኃላፊነት

### ፫. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

፩. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በዘርፉ በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

፪. የግዥ ስራን እንዲያከናውኑ የሚመደቡ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች ጥሩ ሥነ- ምግባር ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

፫. የግዥ ስራን እንዲፈፅም የሚደራጀው ዳይሬክቶሬት ስራውን በቡድን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ስልጣን ያለውና ግልፅ የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋለት መሆኑን ማረጋገጥ፣

፬. የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ከሦስት እስከ አምስት የሚደርስ አባላት ያሉት፣ የመ/ቤቱን ከፍተኛ ግዥዎች መርምሮ የሚያፀድቅ እና ከሦስት ዓመታት የማይበልጥ የአገልግሎት ዘመን የሚኖረው እስከተቻለ ድረስ ፣

ሀ/ በመ/ቤቱ ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ፣

ለ/ በተቻለ መጠን ከተለያየ የሙያ ዘርፍ የተውጣጡ እና በመ/ቤቱ ስራ የተሻለ እውቀት እና ልምድ ያላቸው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ማቋቋም፣

፭. ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አባላትን የአገልግሎት ዘመን ለአንድ ተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ማራዘም፣

፮. የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ እና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች የተሟሉላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

፯. በግዥ አፅዳቂነት የሚመደቡ ሠራተኞች ለስራው የሚያውሉት ጊዜ የመደበኛ ስራቸው አካል ሆኖ በስራ ፕሮግራሞቻቸው እና ውጤት ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ፣

፰. በግዥ ስራ እና በግዥ አፅዳቂነት ለተመደቡ ሠራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች መንግስት ያወጣውን የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ፣ የግዥ አፈፃፀም ማኑዋል፣ መደበኛ የጨረታ ሠነዶች እና ሌሎች አስፈላጊ የግዥ ሠነዶች እንዲደርሷቸው እና የመንግስት የግዥ ስርዓትን በሚገባ እንዲያውቁ የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣

፱. ለግዥ ስራ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የግዥ ዳይሬክቶሬቱም ሆነ አፅዳቂ ኮሚቴው ስራቸውን በተገቢው ለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ፣ እንደአስፈላጊነቱም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

፲. ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዚያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም፣

፲፩. የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመ/ቤቱን የግዥ እቅድ መርምሮ ማፅደቅ፣

ሀ/ የግዥ እቅዱ ከመ/ቤቱ የስራ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣሙን፣

ለ/ ተሰባስበው ሊፈፀሙ የሚችሉ ግዥዎች አንድ ላይ መሰባሰባቸውን፣

ሐ/ ኤጀንሲው በሚወስነው መሠረት ከሌሎች መ/ቤቶች ግዥዎች ጋር ተጣምረው በማዕቀፍ ስምምነት ሊፈጸሙ የሚችሉ ግዥዎች መለየታቸውን፣

መ/ እቅዱ የመ/ቤቱን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ ያካተተ እና ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ የኮሚቴውን ይሁንታ ማግኘቱን፣

፲፪. ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር ተጠቃለው በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀሙ የመ/ቤቱ ግዥዎች፡-

ሀ/ ግዥውን እንዲፈፅም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚፈለጉ መረጃዎች ማለትም እንዲገዛለት የሚፈልገውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዝርዝር መግለጫ፣ለግዥው የያዘውን በጀት መጠንና ምንጭ እንዲሁም ለመረከብ የሚፈልግበትን ጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሟልተው በወቅቱ እንዲላኩ ማድረግ፣

ለ/ ግዥውን እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ግዥውን ለመፈፀም ባወጣው ግልጽ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የገባው ውል ቅጂና ሌሎች ርክክብ ለመፈፀም መሠረት የሚሆኑ የጨረታ ሠነዶች ቅጂ ለመ/ቤቱ መድረሱንና መ/ቤቱም የውል አፈፃፀሙን ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፣ የውሉ አፈፃፀም ላይ ችግር ካለም ወዲያውኑ ግዥውን ለፈፀመው አካል በፁሁፍ ያሳውቃል፡፡

ሐ/ ግዥውን እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ግዥውን ለመፈፀም ባዘጋጀው የጨረታ ሠነድ መሠረት አቅርቦቱ መቅረቡን አረጋግጦ ርክክቡ እንዲፈፀም የሚያደርግ ባለሙያ አዘጋጅቶ ወይም ግዥ ፈፃሚው አካል እንዲመድብለት በማድረግ ርክክቡ መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

፲፫. በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፬ መሠረት በግዥ አፈጻጸም ሂደት የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎችን አግባብነት የማረጋገጥ፣

፲፬. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፪ መሠረት በመ/ቤቱ የተከናወነውን የግዥ አፈጻጸም አስመልክቶ የቀረበ የመረጃ ፍላጎት ጥያቄ በግዥ ዳይሬክቶሬት ተቀባይነት በማጣቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሠጣል፣

፲፭. የውል ሰነድ ይፈርማል፣ በውሉ መሰረትም ግዥው መፈፀሙን ይከታተላል፣

፲፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲፭ ላጁ □ተቶለና□ እንደተጠበቀ ሆኖ በዞን፤ልዩወረዳ፤ወረዳና ከተማ አስተዳደር ባለው መዋቅር በአንድ ፑል ለታቀፉ ሴክተር መ/ቤቶች በተመደበ በጀት ለሚሰሩ የግንባታ ሥራዎች የሚገባ የግዥ ውል በሴክተር መ/ቤቱ የበላይ ኃላኝ ጁ□ረማል፣ ግዥው በውሉ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ በመ/ቤቱ ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ደጋፊ ሥራ ሂደት ክትትል ይደረጋል፣

፲፯. በአዋጁ አንቀፅ ፰/ረ/ መሠረት ከግዥው ውስብስብነት ወይም መ/ቤቱ ካለው የግዥ አቅም በላይ በመሆኑ ምክንያት የመ/ቤቱ ግዥ የሚከተሉትን ተመርኩዞ በሶስተኛ ወገን እንዲፈፀም ሊያደርግ ይችላል፣

ሀ/ ከሶስተኛ ወገን የሚያገኘው የግዥ አገልግሎት አዋጁን እና ይህንን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈፀም ያደርጋል፣

ለ/ ለመ/ቤቱ ግዥ በሚፈፅመው ፫ኛ ወገን እና በመ/ቤቱ መካከል ግልፅ የሆነ የስራ ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል፣

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሰረት በ፫ኛ ወገን ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎች በሙሉ በቅድሚያ ለመ/ቤቱ ቀርበው የተፈቀዱ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፲፰. በበጀት ዓመቱ በመ/ቤቱ የተከናወኑ ግዥዎችን የሚገልጽ የግዥ አፈፃፀም ሪፖርት በአባሪ ቁጥር ፪ ላይ በተገለፀው ቅጽ መሠረት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ወር ቀጥሎ ከሐምሌ 1 እስከ 15 ባለው ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው እንዲላክ ያደርጋል፣

፲፱. የሚከተሉትን ጨምሮ የመ/ቤቱን የግዥ አፈፃፀም በሚመለከት ኤጀንሲው ለሚያደርገው የግዥ ኦዲት ወይም ምርመራ ሥራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ሀ/ ለኦዲት ሥራው የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሚፈለገው ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ለ/ ለተመደቡት ኦዲተሮች አገልግሎት የሚሆን የስራ ቦታ እንዲመቻች ማድረግ፣

ሐ/ ስለተፈፀሙት ግዥዎች አካሔድ ሊያስረዳ የሚችል □ፅዬ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ ማድረግ፣

፳. በግዥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ከኤጀንሲው በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ተገቢ ማስተካከያ የማድረግ እና የተደረጉ ማስተካከያዎችንም ለኤጀንሲው ማሳወቅ፣

፳፩. ከመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለአቅራቢዎች የተፈጸሙ ክፍያዎችን በሚመለከት መረጃው ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል፣

፳፪. በዚህ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አባሪ ቁጥር ፰ ላይ በተገለፀው መሠረት ከሚሰይማቸው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሰብሳቢና ፀሐፊ በተጨማሪ ሰብሳቢው በማይኖርበት ወቅት ሰብሳቢውን ተክቶ የሚሰራ ምክትል ሰብሳቢ በቋሚነት ይሰይማል።

# ፯. የግዥ ፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## ፯.፩ የግዥ ዳይሬክቶሬት እና የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ ዳይሬክቶሬት እና የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ቀጥሎ የተገለጹት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

፩. የመ/ቤቱን ፍላጎት በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ ፰-፲፫ በተገለፀው መሠረት በጋራ ግዥ እንዲፈጽም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚፈፀሙ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በመሆናቸው ምክንያት ከለያቸው በስተቀር መ/ቤቱ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አቅርቦ የኮሚቴውን ይሁንታ ካገኘ በኋላ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

፪. በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩"ሰ"፣ "ሸ" እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ ፯ ከተፈቀደው በስተቀር ማንኛውም የመንግስት ግዥ በአቅራቢነት ከተመዘገቡ እና የባንክ ሂሳብ ካላቸው አቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፫. ከጠያቂ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የጨረታ ሰነድ አዘጋጅቶ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፣

፬. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ በሚሰጡ አስተያየቶች መሠረት የጨረታ ሰነዶችን ያስተካክላል፣

፭. □ፊ ረታ ማስታ□ቂጸ ጸ□□ል፣

፮. የጨረታ ሰነድ ይሸጣል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ፣

፯. የመጫረቻ ሰነድ መቀበያ ሳጥን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣

፰. ጨረታ ይከፍታል፣ እስከተቻለ ድረስ የግዥ ጠያቂው ዳይሬክቶሬት ተ□ካጁ በፊ ረታ አከፋፈት ስነ ሥርዓት ላይ እንዲገኝ ይጋብዛል ፣

፱. በቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ዋና ዋና ገፆች ላይ ማህተም እየተደረገ መፈረሙን ያረጋግጣል፤ የጨረታ መክፈቻ ቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣

፲. የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን ለመንግሥት ገቢ ያደርጋል ወይም ተመላሽ ያደርጋል፣

፲፩. የመጫረቻ ሰነዶች ኮፒዎች ጨረታውን እንዲገመግሙ ለተወከሉ አባላት መሰጠ ታቸውን እና ኦርጅናል ሰነዶቹ ለማጣቀሻነት በጥንቃቄ ተነጥለው መያዛቸውን ያረጋግጣል፣

፲፪. የመጫረቻ ሰነዶችን በቡድን በመሆን ይገመግማል ወይም እንዲገመገም ያደርጋል፣የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ ፳፬.፪ ላይ ከተጠቀሰው በላጁ በመሆኑ ምክንያት የግምገማ ውጤቱ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ መፅደቅ ያለበት ከሆነ ለኮሚቴው ያቀርባል፣(የገምጋሚ ቡድኑ አባላት ቁጥር  ከ3 ማነስና ከ5 መብለጥ የለበትም)

፲፫. የመጫረቻ ሰነድ በግዥ ዳይሬክቶሬት ሲገመገም መረጃዎች በትክክል መገልበጣቸውን፣ የሂሳብ ስሌት በትክክል መሰራቱን ወይም አንድን ተጫራች ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ተግባር አለመፈፀሙን ያረጋግጣል፣

፲፬. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚፀድቁ ግዥዎችን በሚመለከት ከኮሚቴው ለሚቀርቡ የማብራሪያ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፲፭. በሦስተኛ ወገን የሚከናወኑ ግዥዎችን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

፲፮. በዚህ መመሪያ  ንዑስ አንቀጽ ፳፬.፪ ላይ ከተጠቀሱት የገንዘብ ገደቦች በታች የሆኑ ግዥዎችን ያፀድቃል

፲፯. ለአሸናፊ እና ተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ውጤትን ያሳውቃል፣

፲፰. በውል ረቂቅ ላይ ከአቅራቢዎች ጋር ይደራደራል፣ በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ እንዲፈረም ያደርጋል፣

፲፱. የጋራ ግዥ ፈፃሚው አካል ከተለያዩ የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች የቀረቡለትን የግዥ ፍላጎቶች በማሰባሰብ በማዕቀፍ ግዥ ለመፈፀም ባወጣው ግልጽ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የገባውን ውል ጨምሮ መ/ቤቱ በፈፀመው ግዥ የገባቸውን ውሎች

አፈፃፀም በተመለከተ መ/ቤቱ በውል ስምምነቱ መሰረት ግዴታውን መወጣቱን እና የውል መብቱ መከበሩን ያረጋግጣል፣

፰. በጨረታ በሚፈፀሙ ግዥዎች በሙሉ በአሸናፊነት የሚመረጡት አቅራቢዎች አሸናፊ የሆኑበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፰፩. ለጋራ ግዥ ፈፃሚው አካል ያቀረባቸውን የግዥ ፍላጎቶች በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፰፮ ንዑስ አንቀጽ ፲ እና ፲፩ ላይ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ይፈጽማል፣

፰፪. የግዥ ሰነዶችን ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ከሚመለከታቸው ሕጋዊ አካላት ማብራሪያ ሲጠ የቅ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፣

፰፫. በአዋጁ አንቀጽ ፰፫(፪) በተገለጸው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመ/ቤቱን የግዥ አፈጻጸም ሂደት አስመልክቶ መረጃ እንዲሰጠው ጥያቄ ለሚያቀርብ አካል የተጠየቀውን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ይሰጣል:: ሆኖም መረጃውን የመስጠት ሂደት መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርገው ከሆነ መረጃ ፈላጊው ወጪውን እንዲሸፍን መደረግ ይኖርበታል::

## ፮.፪ በክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውስጥ የተደራጀው የጋራ ግዥና ንብረት ማስወገድ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

፩. ከክልሉ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች ተሰባስበው በቢሮው ግዥ እንዲፈፀሙ በሚመለከተው አካል ተለይተው የተሰጡትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ግዥ ለመፈፀም በመመሪያው አንቀጽ 9 መሠረት ፍላጎቶችን ይሰበስባል፣ ይለያል፣ ያደራጃል፣

፪. አመታዊ የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በአጽዳቂ ኮሚቴ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርቦ ያፀድቃል፣

፫. የጨረታ ሠነድ በማዘጋጀት ለአጽዳቂ ኮሚቴ አቅርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

፬. ጨረታ ያወጣል፣

፭. የመጫረቻ ሠነድ መቀበያ ሳጥን ያዘጋጃል፣በሳጥን መቀበል የማያስችል ሲሆን ሠነዱን በኃላፊነት ተቀብሎ የሚጠብቅ አካል ይመድባል፣

፮. ለጨረታው የቀረቡ የመጫረቻ ሠነዶችን መዝግቦ ሳጥን እንዲገቡ ያደርጋል ወይም ይቀበላል፣

፯. ጨረታ ይከፍታል፣ ይገመግማል፣የውሳኔ ሀሳቡን ለአጽዳቂ ኮሚቴ በማቅረብ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

፰. የጨረታ ግምገማ ውጤትን ለአሸናፊና ተሸናፊ ተጫራቾች በደብዳቤ ያሳውቃል፣

፱. የውል ሠነድ አዘጋጅቶ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር እንዲፈራረም ለቢሮው ኃላፊ ያቀርባል፣

፲. ግዥ እንዲፈፀምላቸው ፍላጎት ያቀረቡ መ/ቤቶች ግዥውን በጨረታ ሠነዱና በውሉ መሠረት መሆኑን አረጋግጠው መረከብ እንዲችሉ ለጨረታው የተዘጋጀውን የፍላጎት መግለጫ ሠነድ፣ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር የተገባውን የውል ሠነድና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችና ማስረጃዎችን ለመ/ቤቶቹ ይልካል፣

፲፩. ከአሸናፊው ተጫራች ጋር የተገባውን ውል አፈፃፀም ይከታተላል፣ይቆጣጠራል ወይም ያስተዳድራል፣

፲፪. አቅራቢው በገባው ውል መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ በውሉ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ኤጀንሲው እርምጃ እንዲወስድበት የጥፋተኝነት ሪፖርት ያቀርባል፣

፲፫. ስለፈፀመው ግዥ በሚመለከታቸው አካላት እንዲያብራራ ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፣

፲፬. ግዥ የፈፀመባቸውን ሠነዶች በተፈፀሙበት ቅደም ተከተል መሠረት በፋይል አደራጅቶ በመያዝ የሚመለከታቸው አካላት ለኦዲት ሲጠይቁ አቅርቦ ያስመረምራል፣

፲፭. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፮ የተዘረዘሩትን የአሰራር ሥርዓቶች ተከትሎ ግዥውን ይፈጽማል ፡፡

## ፯. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

፩. በግዥ ዳይሬክቶሬት በተዘጋጀው አመታዊ ዕቅድ፣

ሀ/ የተለዩት የግዥ ፍላጎቶች ከመ/ቤቱ ፕሮግራሞች ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን፣

ለ/ እያንዳንዱን ፍላጎት ለማሟላት ከግዥ የተሻለ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን፣

ሐ/ እቅዱ ግዥን በጥቅል ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን፣እንዲሁም ሌሎች ከመሥሪያ ቤቱ ልዩ ባህርይ አንፃር ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ አስተያየቱን ይሠጣል፣

፪. በግዥ ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጣል፣

ሀ/ በኤጀንሲው ለየግዥው አይነት የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ የተከተለ መሆኑን፣

ለ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን፣

ሐ/ የመወዳደሪያ መስፈርቶቹ አድሏዊ ያልሆኑ፣ ግልፅ እና ተደራሽ መሆናቸውን፣

መ/ ተገቢ ቅፆችን፣በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት እንደግዥው ዓይነት ሊገለጹ የሚገባቸውን ሁኔታዎች እና ሌሎችንም መሠረታዊ ጉዳዮች ማሟላቱን፣

፫. የሚከተሉትን የማጣራት ሥራዎች በማከናወን በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ እንደግዥው ዓይነት ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ ግዥዎች የግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣

ሀ/ ግምገማው በወጣው የጨረታ ሰነድ መሰረት መሰራቱን፣

ለ/ የግዥ አዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የጠበቀ መሆኑን፣

ሐ/ የግዥው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ የተከናወኑት ዝርዝር ግምገማዎችና አጠ ቃላይ የግዥ ሂደቱ መ/ቤቱ ለሚከፍለው ክፍያ ተመጣጣኙን ዓቅም ለማስገኘት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣

፬. በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ ፲፯.፳፫ ላይ የተገለጸውን ተግባራዊ ያደርጋል፣

፭. በቀረበው የግዥ ግምገማ ሪፖርት ላይ የሚሰጥ ማንኛውም አይነት የኮሚቴው ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል፣

፮. አዋጁን፣ የአፈፃፀም መመሪያውን እና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወጡ የአፈጻጸም ሥርዓቶች በተሻለ ሁኔታ ሊፈጸም የሚችልበትን አሰራር ለኃላፊው ያማክራል፣

፯. በኮሚቴው ስለተከናወኑ የግዥ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚገልጽ ሪፖርት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

፰. በመ/ቤቱ የግዥ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ በኮሚቴው ስለተወሰኑ ውሳኔዎች በመ/ቤቱ ኃላፊ ፣በኤጀንሲው ወይም በሌላ ሥልጣን ባለው አካል ሲጠየቅ ማብራሪያ ይሰጣል፣

፱. የአፅዳቂ ኮሚቴው ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖራቸው ዝርዝር የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት እንዲሁም የስብሰባ ስነ - ስርዓት በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፭ ላይ ተመልክቷል።

# ክፍል ፫

## የግዥ ዕቅድ

### ፰. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

፩. ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤትና በሥሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ግዥ በወቅቱ ለመፈፀም የሚያስችል በመርሐ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪. የሚዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

ሀ/ በአዋጁ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከቱትን የመንግስት ግዥ መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣

ለ/ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ ፕሮግራም ለማሳካት፣

ሐ/ የቁጥቁጥ ግዥን በመከላከል የመሥሪያ ቤቱ አሰራር ጊዜና ወጪን ቆጣቢ ለማድረግ፣

መ/ በግዥ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በቅድሚያ በመገንዘብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ፣

፫. የክልሉ መንግስት በተለያዩ ምክንያቶች ለመ/ቤቶች በሚያወርዳቸው በዕቅድ ያልተያዙ ደራሽ ሥራዎች ምክንያት ሰኔ ወር ላይ ግዥ እንዲፈፀም የሚያስገድድ ሁኔታ ካልተከሰተ በስተቀር ማንኛውም የክልሉ መንግስት መ/ቤት ሰኔ ወር ላይ ግዥ መፈፀም አይችልም፡፡

### ፱. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት

፩. ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል፡-

ሀ/ ፍላጎቱ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሐብት ወይም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተና መሥሪያ ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ በተለይ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ያገናዘበ መሆኑን፣

ሠ/ አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ስታንዳርድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ረ/ የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፪. ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በስሩ ከሚገኙ ዳይሬክቶሬቶች የግዥ ፍላጎቶች በማሰባሰብ ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት፡፡

ሀ/ በመ/ቤቱ የሚገኙ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

ለ/ ከተጠቃሚዎች የቀረበውን ፍላጎት በግዥ ዓይነት፣ ብዛት፣ የጥራት ደረጃ እና የሚገኝበትን ቦታ መለየት፣

ሐ/ መ/ቤቱ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራና አገልግሎቶችን መለየት፣

መ/ የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

ሠ/ በመ/ቤቱ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለየግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣

ረ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ መዘጋጀቱን ወይም ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ማረጋገጥ፣

፫. የመንግስት መ/ቤቶች ከተጠቃሚዎች የተሰባሰበውን ፍላጎት፣ ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ፍላጎታቸውን ማደራጀት አለባቸው:-

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ፣አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም ፶% (ሃምሳ በመቶ) በላይ ድርሻ ያለውን የግዥ ዓይነት መሠረት በማድረግ መፈፀም፣

ለ/ እስከተቻለ ድረስ ተቀራራቢ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶችን በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣

ሐ/ በአንድ ላይ ለሚፈፀሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ አይነት በተለያየ ምድብ /ሎት/ በመከፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ/ ግዥው ለአፈጻጸም አመቺ እና አደናቃፊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሠ/ እስከተቻለ ድረስ የአገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር እድልን በሚያሰፋ መልኩ ግዥው እንዲደራጅ ማድረግ ።

፬. ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለሚፈጽሙት ግዥዎች የሚያስፈልገውን በጀት ለመወሰን እና በጨረታ በሚፈጽሙት ግዥ አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች አሸናፊ የሚሆንበት ዋጋ የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲያስችላቸው የገበያ ዋጋ ጥናት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ሀ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለሚፈፀሙ ግዥዎች የሚያሰፈልገውን በጀት ለመወሰን የሚገለገሉበት የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ወቅት የተጠና፣ እንዲሁም በጨረታ አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች አሸናፊ የሚሆንበት ዋጋ የወቅቱ የገበያ ዋጋ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚገለገሉበት የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተጠና የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ መሆን ይኖርበታል።

ለ/ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች የገበያ ዋጋ ለማጥናት የሚገለገሉበት ሠነድ ለመግዛት ስለሚፈልጉት ዕቃ ዝርዝር የቴክኒክ መግለጫ ለአቅራቢዎች የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል።

## ፲. የግዥ ዘዴ መምረጥ

፩. የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በአዋጁና በዚህ መመሪያ ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን በመምረጥ በዕቅዱ ላይ ማመልከት አለባቸው።

፪. የመንግስት መ/ቤቱ የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች ሁሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱም ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለበት።

## ፲፩. የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን

፩. የመንግስት መ/ቤቶች ለግዥ እቅድ ማዘጋጃ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ቅፅ በመጠቀም በግዥ ሂደቱ ውስጥ ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወኑበትን ጊዜ መወሰን አለባቸው። ለዚህም የሚከተሉትን እና ሌሎች እንደሚፈፀመው የግዥ ዓይነት አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል።

ሀ/ ግዥው የሚከናወንበት ጊዜ ከመስሪያ ቤቱ የሥራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

ለ/ በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

ሐ/ በ□ህ መመሪያ አባሪ ቁዓር ፫ ላይ በተገለፀው መሠረት ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀ እና እስከተቻለ ድረስ ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ማዘጋጃ ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፣

መ/ በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዓይነቱ የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈጻጸም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

## ፲፪. የግዥ ዕቅድ ይዘት

፩. የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ ክፍል ፫ ላይ የሠፈሩትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ እና በ□ህ መመሪጸ አባሪ ቁዓር ፩ ላይ በተመለከተው የግዥ ዕቅድ ማዘጋጃ ቅፅ በመታገዝ የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው። በዚህ መሰረት የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

ሀ/ የግዥውን ምድብ ፣ ቁጥር፣

ለ/ የግዥውን መግለጫ፣

ሐ/ የግዥውን መጠን፣

መ/ የግዥው ዝርዝር አፈጻጸም የሚከተላቸው አሠራሮች፣

ሠ/ ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚፈፀሙበትን ጊዜ፣

ረ/ ለግዥው የሚያስፈልገውን በጀት መጠንና የፋይናንስ ምንጭ፣

ሰ/ ለግዥው ተስማሚ የሆነ ውል ዓይነት፣

ሸ/ በግዥ አፈጻጸም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፣

ቀ/ ሌሎች እንደ መ/ቤቱ ባህሪ ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮችን፣

፪. የመንግስት መ/ቤቱ ለግዥ ዕቅድ ዝግጅት በግብዓትነት የተጠቀመባቸውን ዋና ዋና መረጃዎች ምንጭ እና ሌሎች የግዥ ዕቅዱን ለተጠቃሚው የበለጠ ግልፅ ያደርጋሉ ብሎ የሚያስባቸውን መረጃዎች ከግዥ እቅድ ቅፁ ጋር በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

## ፲፫. የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

፩. የግዥ ዳይሬክቶሬቶች ያዘጋጁትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ ለተቋቋመው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አቅርበው አስተያየት ከተቀበሉ በኋላ እቅዱን ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቅርበው ማፀደቅ አለባቸው፡፡

፪. የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፡፡

፫. በመ/ቤቱ  የበላይ ኃላፊ  የፀደቀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ቅጅ  በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ለአፈጻጸም □ፅዴ ፍላጎት ላቀረቡ አካላትና  ለኤጀንሲው በበጀት □መቱ መ□መሪያ እስከ ሐምሌ 30 መላክ አለበት፡፡

፬. በመንግስት መ/ቤቶች የተዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተቀባይነት ካገኘና የዕቅዱ ቅጅ ለኤጀንሲው ከተላከ በኋላ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸሙን መከፋፈል ወይም በዕቅዱ ከተገለጸው አሠራር ውጭ መፈጸም አይችሉም::

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት እና በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሲታመንበት በማንኛውም ጊዜ የግዥ ዕቅዳቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ::

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ በተገለጸው መሠረት የተሻሻለውን የግዥ ዕቅድ የመጀመሪያው ዕቅድ ለተላከላቸው አካላትና ለኤጀንሲው መላክ አለባቸው::

## ፲፬. ዓመታዊ የግዥ እቅድን ይፋ ማድረግ

ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ከመ/ቤቶች የተላከለትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በማሰባሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተገለፀው የገንዘብ መጠን በላይ የሆነን የግዥ ዕቅድ እንደአስፈላጊነቱ በየግዥው አይነት በመለየት ይፋ ያደርጋል:: ወይም መ/ቤቶች የተጠቀሰውን መረጃ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ የሚያወጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

# ክፍል ፬
# የግዥ ዘዴዎችና አፈፃፀማቸው

## ፲፭. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

፲፭.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፴፫ መሠረት የሚከተሉት የግዥ ዘዴዎች ተፈቅደዋል:-

ሀ/ ግልጽ ጨረታ፣

ለ/ ውስን ጨረታ፣

ሐ/ በሁለት ደረጃ ፊ ረታ □ሚ□ናም ዕዴ

መ/ በመ□ቲ□ሪጸ ሃሳብ መ□□ቂጸ □ሚ□ናም ዕዴ

ሠ/ በአካባቢ ማስታ□ቂጸ በመለ□አ □ሚ□ናም ፅዴ

ረ/ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ

፲፭.፪ በአዋጁና በ□ህ መመሪጸ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈጸም አለባቸው::

፲፭.፫ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው::

፲፭.፬ በአዋጁ አንቀጽ ፴፫/፫ በተደነገገው መሠረት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ ይኖርበታል::

## ፲፮. የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ግዥ አፈፃፀም

የመንግስት መ/ቤቶች በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈጸም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም እና በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን አፈፃፀሞች መከተል አለባቸው::

### ፲፮.፩ ቅድመ - ሁኔታዎች

የመንግስት መ/ቤቶች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

፲፮.፩.፩ የሚፈለገውን ግዥ በአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ሊያሟላ መቻሉን እና ግዥው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ለዓለም አቀፍ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በታች መሆኑን፣ ወይም

፲፮.፩.፪ የግዥው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ገደብ በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑን፣

## ፲፮.፪ የጨረታ ጥሪ

፲፮.፪.፩ □ጫ ረታ ጥሪው በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ አገራዊ የስርጭት ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት አለበት::

፲፮.፪.፪ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፪.፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ በመረጠው ጊዜና መጠን በአዋጁ አንቀጽ ፴፳/፪/ በተገለጸው መንገድ እና በሌሎች አገራዊ የስርጭት ሽፋን ባላቸው መገናኛ ብዙሀን ተጨማሪ የጨረታ ጥሪ ሊያስተላልፍ ይችላል::

፲፮.፪.፫ የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል:-

ሀ. □ጫ ረታ□ ጥሪ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደረገው የመንግስት መ/ቤት ስምና አድራሻ፣

ለ. የሚቀርበውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነት፣ ከተቻለ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራዎችን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር አገልግሎት ዓይነት እና የሚሰጥበትን ቦታ፣

ሐ. በፊ ረታ□ መሳተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባውን መሥፈርት፣

መ. የጨረታው ሰነድ የሚገኝበትን ቦታ፣

ሠ. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠን፣

ረ. የጨረታውን ሰነድ ለመውሰድ የሚከፈልን ዋጋ፣እና የአከፋፈሉን ዘዴ፣

ሰ. የመጫረቻ ሠነዱ የመጨረሻ ማስረከቢያ እና የሚከፈትበትን ቀን ፣ቦታና ሰዓት፣

ሸ. የመንግስት መሥሪያቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለመሠረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ እና

ቀ. ለተጫራቾች መገለጽ እንዳለባቸው በመሥሪያ ቤቱ የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

፲፮.፪.፩ የጨረታው ጥሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፮.፲፫ ላይ በተገለፀው መሰረት ጨረታው በሚካሔድበት ቋንቋ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

## ፲፮.፫ የጨረታ ሰነድ

### የመንግስት መ/ቤቶች

፲፮.፫.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ መሠረት ለሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፲፮.፫.፪ □ፊ ረታ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት በኤጀንሲው ከተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሠነድ ውስጥ በተጫራቾች መመሪያ እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳያደርጉ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደግዥው አይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሠነዱን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

፲፮.፫.፫ □ፊ ረታ ሠነድ በዋናነት በግዥ ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ሲሆን፣ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ውሳኔ መሠረት ለሚፈጸም ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

## ፲፮.፩ የተጫራቾች መመሪያ

፲፮.፬.፭ ማንኛ□ּም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጎ ለተጫራቾች መስጠት አለበት፡፡

፲፮.፬.፮ በመ/ቤቶች የሚዘጋጀው የተጫራቾች መመሪያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆኑን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ወይም የግንባታ ስራ፤ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፤ የመንግስት መ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

ለ/ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶች የሚገልፅ ሆኖ ከወጣው ጨረታ ውስጥ ከብር 50,000.00 በላይ ዋጋ ባለው ግዥ የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም የውጭ አገር ተጫራቾች በሚሆኑበት ጊዜ እንደአግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው መጠቀሱን፣

ሐ/ በጨረታ ሰነዱ ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻ፤ ጊዜ እና የማብራሪያ ጥያቄው በፅሑፍ መቅረብ እንደሚገባው የሚያመለክት መግለጫ፣

መ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፤ በምን ቋንቋ እንደሚዘጋጅ፤ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለፁ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች እና ቅፆች አይነት እና ብዛት፣

ሠ/ ተጫራቹ የማጭበርበር ድርጊት እና ሙስናን በሚመለከት፣ በኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገገውን የሚያከብር መሆኑን በማረጋገጥ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ሙሰና ላለመፈፀም ቃል የሚገባበትን ቅፅ እና ሌሎች በተጫራቹ ተሞልተው እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ እንዳለበት፣

ረ/ የጨረታውን አካሔድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ፤ ለወደፊትም በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ የሚያመለክት መግለጫ፣

ሰ/ የዕቃዎቹ ናሙናዎች በተጫራቾች እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትንና እንደፈስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም እነዚህ ናሙናዎች በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፣

ሸ/ የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበትን ቦታ እና ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልፅ መግለጫ፣

ቀ/ ጨረታውን ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች፣ ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፣ እንዲሁም ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳደሪያ ሐሳብ የሚቀርበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

በ/ በውል አፈጻጸም ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ መቻል አለመቻሉን እና የዋጋ ማስተካከያው የሚፈቀድ ከሆነ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ፣

ተ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ፣ የውል አፈፃፀም ዋስትና መጠን እና ዓይነት እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበትን ጊዜ፣

ቸ/ የመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን እና ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት፣

ነ/ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

ኘ/ በአዋጁ ለአገር ውስጥ ምርትና ኩባንያዎች የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈጻጸም የሚያመለክት መግለጫ፣

አ/ ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ኢንቨሎኘ የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ ስለኤንቨሎፖች አስተሻሸግ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋናና ቅጂ ሠነዶች መቅረብ እንዳለባቸው፣ የቅጂዎችን ብዛት፣ ሠነዶቹ ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው ሊሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ እንዲሁም (ወቅታዊ የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት፣ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ሌሎች መ/ቤቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ደጋፊ ሰነዶች) ስለሚቀርቡበት ሁኔታ፣

ከ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮.፳፮ በተደነገገው መሠረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ፣ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን እና የሚቀርበውን ዋስትና አይነት እና መጠን፣

ወ/ ተጫራቾች በጨረታው የአፈፃፀም ሒደት ቅሬታ ካላቸው በግዥ አዋጁ ምዕራፍ አሥራ አራት እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፬ እና ፵፮ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው እና አቤቱታው የሚቀርብበትን ቦታ፣

ዘ/ መ/ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሠነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጨረታ ውድድሩ በአሸናፊው የተሰጠው ዋጋ ሳይቀየር እስከ ፳% (ሃያ በመቶ) መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚችል፣

□ / መ/ቤቱ ለዕጩ ተጫራቾች በጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ ላይ የገለፃቸው የጨረታ ሥነ ሥርዓቶች፣ መስፈርቶችና ሌሎች መረጃዎች በጨረታ ሠነዱ ላይ ከገለፃቸው የሚለዩ ከሆነ በጨረታ ሠነዱ ላይ የገለፃቸው የበላይነት እንደሚኖራቸው መገለፁን፣

፲፮.፬.፫ በመደበኛው ጨረታ ሠነድ የተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም ዓይነት ማሻሻያ ሊደረግ አይቻልም:: ቢሆንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመለከቱት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ነው ::

## ፲፮.፭ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

ሀ/ የመንግስት መ/ቤት በተለይም በተፈጥሯቸው ውስብስብ እና ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቁ ግዥዎች በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ መሠረት ዝርዝር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት አለበት::

ለ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ እንደግዥው ዓይነት ጠቀሜታውን ወይም አሠራሩን ወይም የቴክኒክ ወይም የዲዛይን ባህርይን መሠረት በማድረግ ውድድርን እንዳይገደብ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት::

ሐ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የአቅርቦቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል::

መ/ የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈልገው ክፍል ወይም ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ እውቀት ባላቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች መዘጋጀት አለበት :: ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ እና ውስብስብ በሆኑ ግዥዎች የፍላጎት

መግለጫ አዘገጃጀት ላይ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎች ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊያሠሩ ይችላሉ፣

ሠ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም። ሆኖም ፍላጎትን በትክክል ሊገልፅ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን የሚመለከት ሲሆን ወይም የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችል አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ "ወይም ተመሳሳይ" የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል።

ረ/ የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የመንግስት መ/ቤቱን የአሁን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን የማያካትት መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

ሰ/ የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵጸ ጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል ።

ሸ/ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የተሟላና ትክክለኛ የመጫረቻ ሠነድ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት።

## ፲፮.፮ የጨረታ ቅፅና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቶች ለጨረታ በሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ውስጥ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ወይም እንደግዥው ባህርይ የመንግስት መ/ቤቱ ያዘጋጀውን በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ዋጋና ተያያዥ ጉዳዮችን ማቅረቢያ ቅጽ ወይም ሠንጠረዥ እና በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው።

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በመንግስት መ/ቤቶች የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋን፣ ታክስን እና ሌሎችን ከዋጋ

አቀራረብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በግልፅ ለማመልከት የሚያስችል የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት::

ሐ/ የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳዳሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፣ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፣ ጨረታውን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከል እና ተጫራቹ ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ሙሉ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል::

## ፲፮.፯ አጠቃላይና ልዩ የውል ሁኔታዎች

፲፮.፯.፩ ማንኛ□ም የመንግስት መሥሪያ ቤት የመደበኛ የጨረታ ሠነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን አጠቃላይ እና ልዩ የውል ሠነድ ቅጂዎች የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጐ ለተጫራቾች መስጠት አለበት::

፲፮.፯.፪ በመ□በኛ ጨረታ ሠነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም:: ልዩ የውል ሁኔታውን ግን እንደሚፈፀመው ግዥ ባህርይና ዓይነት አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የሰፈሩትን አንቀጾች በማጣቀስ ማሻሻል ይቻላል::

፲፮.፯.፫ ከላይ ንዑስ አንቀጽ ፲፮.፯ "፩ እና ፪" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች የሚያዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው አይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት:-

ሀ/ የተጫራቹንና የመንግስት መ/ቤቱን ግዴታና ኃላፊነትን በግልጽ ያመላከተና በመ/ቤቱ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ/ እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የማጓጓዝ ኃላፊነት፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ስነ - ስርአት፤ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል::

## ፲፮.፰ የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት አዘገጃጀት

፲፮.፰.፩ የመንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሰነድ የሚገመገምበትን መስፈርት በመደበኛ የጨረታ ሠነዱ የብቃትና የግምገማ መሥፈርቶች ክፍል ላይ በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራዎች ግዥ ላይ የሚጠየቀው የሥራ ልምድና የብቃት መስፈርቶች በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፮ ላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡

፲፮.፰.፪ የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት እንደ ግዥው አይነት የሚለያይ ቢሆንም ከሚከተሉት ሁለት መሰረታዊ የመምረጫ ዘዴዎች በአንዱ ተፈፃሚ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለው ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ/መስፈርት በማስቀመዓ ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካሟሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ፣ ወይም

ለ/ እላዩ በኘ□ል ተራ ሀ □ተ□ቀሰ□ □ቅተኛ መመ□ኛ/መስፈርት መሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥው የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ እሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶችን /መ/ቤቱ ለዋጋና ለቴክኒክ የሚሰጠውን አንጻራዊ ክብደት/ መሠረት በማድረግ ከመቶ የተወሰነ ነጥብ ለዋጋ ቀሪውን □ፅሞ ለቴክኒክ በመስጠትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ በመመስረት ተገምግሞ በሚገኝ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች መምረጥ፡፡

ሐ. ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች እላይ በፊደል ተራ ለ የተጠቀሰውን የመረጣ ዘዴ የሚጠቀሙ ከሆነ ለዋጋና ለቴክኒክ የተሰጠውን የነጥብ ድርሻ፣ ለቴክኒክ ግምገማ የተመረጡትን ዝርዝር መስፈርቶችና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ በሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ውስጥ በማስፈር ተጫራቾች በቅድሚያ እንዲያውቁት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፲፮.፳.፫ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳(፪/ለ) በተገለጸው መምረጫ ዘዴ ለማከናወን ግምገማ እንዲያገለግል የሚመረጥ መስፈርት ግዥው ማስገኘት የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ከማድረግ አንፃር በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተና እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የሚገዛው መደበኛ ወይም ደረጃው የታወቀ አቅርቦት በሚሆንበት ጊዜ ለመ/ቤቱ ጠቃሚ የሆነ እና በተጫራቾች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የሚችል የተለየ እሴት ሊቀርብበት የሚችል መሆን አለመሆኑን፤ ወይም

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴት ተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን ወይም ተጨማሪው እሴት ለመ/ቤቱ የሚሠጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ ደረጃ ያልወጣለትና ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንፃር ስፔሲፊኬሽኑን በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራራቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

መ/ ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያየ የመጠቀሚያ፤ የመጠበቂያና የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፣

፲፮.፳.፬ የመንግስት መ/ቤቱ ተጫራቾች ያቀረቡት ሠነድ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳ በተገለፁት መስፈርቶች መሰረት ከተገመገመ በኋላ የአሸናፊው ተጫራች ብቃት በድሕረ ግምገማ በተጨማሪ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያምን ይህንኑ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሳየት እና ለድሕረ ግምገማው ተፈፃሚ የሚሆነውን መስፈርት መግለፅ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፳.፭ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳ (፫) መሰረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ እና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሰረት አንፃራዊ ክብደት እንዲሰጣቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፰.፮ ፅዴ □ነሚ መ/ቤቶች የሚፈጽሙት የግዥ ዓይነት ዕቃና የግንባታ ሥራ ሲሆን በስራ ላይ መዋል ያለበት የመጫረቻ ሰነድ ግምገማ ወይም መረጣ ዘዴ በንዑስ አንቀጽ ፲፮/፰/፪/ሀ ላይ የተመለከተው መሆን አለበት።

፲፮.፰.፯ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፰.፮ የተገለጸው ቢኖርም መ/ቤቶች በሚፈጽሙት ግዥ ማግኘት የሚፈልጉት ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ ከሌሎች ተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም የግንባታ ሥራዎች የተሻለ የጥራት ደረጃና ጥቅም ያለውን ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ ማፅኘት የሚያስችለኝን የመረጣ ዘዴ መጠቀም አለብኝ ብለው ሲያምኑ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በማስወሰን በንዑስ አንቀጽ ፲፮/፰/፪/ለ ላይ የተመለከተውን የመረጣ ዘዴ መጠቀም ይችላሉ።

፲፮.፰.፰ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች በንዑስ አንቀጽ ፲፮/፰/፯ ላጁ በተቶለና□ ምክንያት ለሚገዙት ዕቃ ወይም የግንባታ ሥራ የሚጠቀሙት የመገምገሚያ ወይም የመረጣ ዘዴ በንዑስ አንቀጽ ፲፮/፰/፪/ለ ላጁ □ተቶለፀውን ሲሆን ለዋጋ ግምገማ የሚሰጡት አንፃራዊ ክብደት ወይም የነጥብ ድርሻ ፹ በመቶ ለቴክኒክ ግምገማ ደግሞ ፳ በመቶ መሆን ይኖርበታል፣

፲፮.፰.፱ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ከ፸ በታች ያመጡ ተጫራቾች ውድቅ ተደርገው ከመቶ ፸ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡ ተጫራቾች ብቻ ለዋጋ ግምገማ መቅረብ ይኖርባቸዋል፤፤

፲፮.፰.፲ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ እና በዋጋ ግምገማ ተጫራቾች ያመጡትን ውጤት በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘ□ ተ□ቴቴሪ □ፌ ረታው አሸናፊ ተ□ር□ ጁመረ□ል፣

፲፮.፰.፲፩ ለቴክኒክ ግምገማው የሚመረጡት ዝርዝር መስፈርቶች እንደግዥው ዓይነት የተለያየ በመሆኑ በግዥ ፈጻሚው መ/ቤቶች የሚመረጡ ሆኖ መ/ቤቶቹ ካስቀመጡት ዝቅተኛ መስፈርት መተጨማሪነት የሚያስገኙት ተጨባጭ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መኖርና አለመኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸኸል፣

፲፮.፰.፲፪ ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በሥራ ላይ የሚ□ለው የግምገማ ዘዴ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፰ (፪/ለ) ላይ የተመለከተው ሲሆን፣ ለዋጋ የሚሰጠው አንፃራዊ ክብደት ከጠቅላላው የማወዳደሪያ ነጥብ ፶% /ሃምሳ በመቶ/ ማነስ የለበትም። በሌሎች

አገልግሎቶች ከሚካተቱት አገልግሎቶች ውስጥ በ□ህ መመሪጸ አባሪ ቁዓር ፫ ተራ ቁዓር ፩.፪ ላጁ □ተ□ረ□ሩት ጁቶኙበታል::

## ፲፮.፱ ጨረታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን

፲፮.፱.፩ የመንግስት መሥሪያ ቤት የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሠነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል:-

ሀ/ ተቀባይነት ያለው የመጫረቻ ሠነድ ለማዘጋጀት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን እና ሌሎች ለጨረታው የሚፈለጉ እንደ ሽርክና መመሥረት፣ ከአምራቹ የሚሠጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ እና የመሳሰሉትን ለማውጣት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሠነዱን ለማግኘት እና ያዘጋጁትን የመጫረቻ ሠነድ ለማድረስ የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ፣

ሐ/ በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ ለግንባታ ቦታ ጉብኝትና ከጨረታ በፊት ለሚደረግ ቅድመ ጨረታ ውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

፲፮.፱.፪ በንዑስ አንቀጽ (፲፮.፱.፩) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታ አየር ላይ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ላሉት ተከታታይ ቀናት ሲሆን በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፫ ላይ ከተገለፀው ቀን ያነሰ መሆን የለበትም::

## ፲፮.፲ የጨረታ ሠነድ ሽያጭ

፲፮.፲.፩ ለማንኛውም ጨረታ የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ የመሸጫ ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ ፴፰ መሠረት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት በመንግስት መ/ቤቶች የሚወሰን ይሆናል:-

ሀ/ የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ የመንግስት መ/ቤቱ ለግዥው በርካታ ተወዳዳሪዎች እንዳያገኝ የሚያደርግ መሆን የለበትም፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች ለማንኛውም የጨረታ ሠነድ የዋጋ ተመን በሚወስኑበት ወቅት ትርፍን ማዕከል ያላደረገና ለሰነድ ዝግጅቱ የወጣውን ወጪ ለመተካት ብቻ ያለመ መሆን ይኖርበታል።

፲፯.፲.፪ የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ሠነዱ በነፃ እንዲሠጥ ወይም ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ለተጫራቾች እንዲሸጥ ሊፈቅዱ ይችላሉ:-

ሀ/ በጨረታው በቂ ተወዳዳሪ አይኖርም ተብሎ ሲገመት፣ ወይም

ለ/ ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት በጣም አነስተኛ ነው ብሎ መ/ቤቱ ሲያምን፣ ወይም

ሐ/ ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ተጫራቾች እንዲሸፍኑ ቢደረግ የጨረታ ሰነዱ የመሸጫ ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን በቂ ተወዳዳሪ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል ብሎ ሲያምን፣

መ/ ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ የተደረገ እና በመጀመሪያው ጨረታ ለመሳተፍ ሰነድ የገዙ እጩ ተወዳዳሪዎችን እንደገና እንዲገዙ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑ በመ/ቤቱ ሲታመን፣

፲፯.፲.፫ □ፊ ረታ ሠነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት።

## ፲፯.፲፩ ስለ ናሙና አቀራረብ

፲፯.፲፩.፩ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይም እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል።

፲፮.፲፩.፪ የመንግስት መ/ቤቱ ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለዕይታ በቀረበው ናሙና መሠረት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት:-

ሀ/ በመንግስት መ/ቤቱ የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም:: እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች አይነት ለእይታ እንዲቀርብ ሆኖ ሌሎች ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያላቸው ዕቃዎችን ማቅረብ እንደሚችሉ ተጫራቾች እንዲያውቁት ማድረግ ይገባል::

ለ/ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ የሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሐ/ መ/ቤቱ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅ መሆን ያለበት ሲሆን የቀረበው ናሙና ካለው የቴክኒክ ባሕርይ ውጪ ያለ ባሕርይ በቴክኒክ መግለጫው ውስጥ እንዲካተት ሊደረግ አይገባም::

፲፮.፲፩.፫ በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሰረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት:-

ሀ/ የሚቀርቡት ናሙናዎችን አይነት፣ ብዛት የሚቀርቡበት ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

ለ/ ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ ያለባቸው ቢሆንም ዕጩ ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ ከዕጩ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በማጓጓዝ ሂደት ቢዘገይ የመንግስት መ/ቤቱ የግዥውን አፈፃፀም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል::

፲፮.፲፩.፬ ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት የመንግስት መ/ቤቱ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቀድ ይችላል:: ይህም የናሙናውን

ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሒደት ልዩነት የማያመጣ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

፲፮.፲፩.፫ የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በዕቃው ባህርይ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም፡፡ በምርመራ ሂደት ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ከምርመራ በኋላ ለተጫራቾች ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡ ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታው ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልወሰዱ በውርስ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

፲፮.፲፩.፬ በመንግስት መ/ቤቱ የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊው ተጫራች ናሙና ግዥው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል መደረግ ይኖርበታል፡፡

## ፲፮.፲፪ በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

፲፮.፲፪.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፴፱ መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄን ተቀብለው ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

፲፮.፲፪.፪ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፪.፩ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተለውን ሳያሟላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ መሥሪያ ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም፡-

ሀ/ በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሰረት ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ፴ ቀናት ለሆነ ውስብስብ የአገር ውስጥ ግዥ የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ፲ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ለ/ ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የተወሰነው ጊዜ ሊያበቃ ከ፳፩ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

ሐ/ ጨረታው ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ፲፭ ቀናት ብቻ ለሆነ ውስብስብ ያልሆነ ግዥ ጨረታው ሊዘጋ ከ፭ ቀናት በታች ሲቀረው ለቀረበ ጥያቄ፣

፲፮.፲፪.፫ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ለሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄ የሚሠጠው ምላሽ በጽሑፍ ሆኖ የጠያቂውን ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለመሆን ላመለከቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎቸ በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ እንዲላክ መደረግ አለበት፡፡

፲፮.፲፪.፬ የመንግስት መ/ቤቶች ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የጨረታ ሠነዱን ማሻሻል ይችላሉ፡፡ የተሻሻለው ወይም ማንኛውም የጨረታ ሠነዱን ይዘት የሚቀይር ሰነድ፤ ማሻሻያ በሚል በተሻሻለ ተጨማሪ የጨረታ ሠነድነት የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ሁሉ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

፲፮.፲፪.፭ የመንግስት መ/ቤቶች በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፪.፬ ላይ በተገለፀው መሰረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም ይኖርባቸዋል፡፡

፲፮.፲፪.፮ የመንግስት መ/ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የጨረታ ሠነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ የማብራሪያና የማሻሻያ ገለጻና ውይይት ለማድረግ ሊጠራ ይችላል፡፡ የሚደረገው ውይይትም በቃለ -ጉባዔ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፪.፯ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ማሻሻያውን ማካተት እንዲችሉ በተደረገው የጨረታ ሠነድ ማሻሻያና ማብራሪያ ውይይት

ላይ የተያዘው ቃለ - ጉባዔ ቅጂ ለሁሉም የጨረታውን ሠነድ ለገዙ ዕጩ ተጫራቾች እንዲደርስ መደረግ አለበት::

## ፲፮.፲፫ የጨረታ ቋንቋ

፲፮.፲፫.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ መሠረት የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ሠነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ፣

ሀ/ የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ ይሆናል:: ሆኖም መ/ቤቱ የጨረታ ቋንቋው በእንግሊዝኛ መሆኑ የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሠነዱ፣ እና የጨረታው ሂደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል::

ለ/ ለዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ ማስፈጸሚያ የሚዘጋጅ ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይሆናል::

፲፮.፲፫.፪ ከላይ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሠነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ በሚሆንበት ጊዜ በተለይ የጨረታውን መሠረታዊ ይዘት ሊቀይሩ የሚችሉ ሠነዶች በሕጋዊ ተርጓሚ ከተተረጎመ ቅጂ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ማቅረብ አለባቸው::

፲፮.፲፫.፫ የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበው ሠነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ ለውጥ አያመጣም ብሎ ካላመነ በስተቀር ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል::

## ፲፮.፲፬ የፌ ረታ□ ዋጋ እና የዋጋ ማስተካከያ

፲፮.፲፬.፩ የመንግስት መ/ቤት ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱ እና በጨረታው እና በውል አፈፃፀሙ ወቅት የማይለዋወጡ ፅኑ ዋጋ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፲፮.፲፬.፪ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፬.፩ ላይ የተገለፀው ቢኖርም፣ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ ለግንባታ ስራዎች ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ፲፪ ወራት በኋላ እና በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ፫ ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል:-

ሀ/ በውል ስምምነቱ መሰረት የግንባታ ስራውን ለማጠናቀቅ ከ፲፰ ወራት እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ ከ፮ ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፣

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም የጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣

መ/በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፬.፪ (ሐ) የተገለጸው ቢኖርም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መስጠት ባልቻሉባቸው ስብስቦች ላይ የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸውን ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል፣

ሠ. በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ተሰ□ ተብሎ □ቀረበ□ □ቅታዊ □ዥፉ ኢንዴክስ መረጃ ትክክለኛነት በ□ልሉ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሲረፉቶዓ ፣

፲፮.፲፬.፫ ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤

በንዑስ አንቀጽ ፲፯.፲፬.፪ የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት ይኖርበታል፡-

ሀ/ ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣

ለ/ በሥራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን ፣

ሐ/ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለው የዋጋ ኢንዴክስ/ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

መ/ የዋጋ ማስተካከያው ጥያቄ በንዑስ አንቀጽ ፲፯.፲፬.፪ ላይ የተገለጸውን ድንጋጌ ተከትሎ በሚቀርብበት ወቅት በተለይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ልዩነቱ የሚሰላው በሥራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ/ ጠቋሚ አሃዝን በመጠ ቀም በቀመሩ መሠረት ይሆናል፣

## ፲፯.፲፬.፫ በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ □ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን አለበት።

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከ፲ ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል።

ሐ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ

የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ መገለፅ አለበት፡፡

መ/ የመንግስት መ/ቤቱ በውሉ ላይ በተገለፀው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈፃሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፡፡

ሠ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

## ፲፯.፲፬.፭ ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፤

ሀ/ በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መ/ቤቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ለ/ በንዑስ አንቀጽ ፲፯.፲፬.፭ (ሀ) የተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአሥራ አምስት ከመቶ (፲፭%) ሊበልጥ አይችልም፡፡

፲፯.፲፬.፮ መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ አይነት፣

ለ/ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዞው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን አይነትና መጠን፣

ሐ/ ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

፲፮.፲፬.፯ የመንግስት መ/ቤቱ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፬.፰ የመንግስት መ/ቤቱ እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልፅ እንዲካተቱ መደረግ ይኖርበታል:-

ሀ/ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያውን አፈፃፀም፣

ለ/ ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም የመንግስት መ/ቤቱ እና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ አይነት እና ምንጭ፣

ሐ/ ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለፀው መሠረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣

መ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ስራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠር የዋጋ መናር ማስተካከያ የማይደረግበት ስለመሆኑ፣

፲፮.፲፬.፱ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠ ረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ ፳፭% (ሃያ አምስት ከመቶ) በሚበልጥበት ጊዜ የመንግስት መ/ቤቶች □ዥዥ ለውጡን □አጸ ከመፈፀማቸው በፊት ለ□ልሉ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማቅረብ ማስፈቀድ አለባቸው፡፡ ኤጀንሲውም መ/ቤቱ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝለት ወይም የማያስገኝለት መሆኑን በአግባቡ በመገምገም ይወስናል፡፡

፲፮.፲፬.፲ የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ

እንዲደረግባቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብአቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል ይኖርበታል።

## ፲፮.፲፫ የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

፲፮.፲፫.፩ የመንግስት መ/ቤቱ የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል። የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው አይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጊዜውን ለመወሰን መ/ቤቱ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርበታል፡-

ሀ/ የግዥውን ውስብስብነት እና የጨረታ አፈፃፀም ሂደቱ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣

ለ/ በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ብዛት፣

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ረገድ ያለው ልምድ፣

መ/ ግዥው በገበያ ላይ ያለውን የዋጋ ተለዋዋጭነት ሁኔታ፣

፲፮.፲፫.፪ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፫.፩ ላይ በተገለፀው መሰረት የሚወሰነው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥውን ለመገምገም፣ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ግዥውን ለማፀደቅ፣ አቤቱታ ቢነሳ ለማስተናገድ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከመፈራረም ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

፲፮.፲፫.፫ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፫.፪ ላይ በተገለፀው መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ረዘም ላለ ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ሁኔታ መኖሩን መ/ቤቱ ካላመነ በስተቀር ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው ከሚከፈትበት ዕለት ጀምሮ ከ፳ ቀናት መብለጥ የለበትም።

፲፮.፲፫.፬ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ሂደታቸውን የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም ይኖርባቸዋል። ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን መ/ቤቱ ሲረዳ ዕጩ

ተወዳዳሪዎች ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት መጠየቅ አለበት።

፲፯.፲፫.፫ በንዑስ አንቀፅ ፲፯.፲፫.፩ ላይ በተመለከተው መሰረት ተጫራቾች እንዲያራዝሙት የሚጠየቁት ተጨማሪ ቀናት የመንግስት መ/ቤቱ የቀረውን የግዥ ሒደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን አለበት። ሆኖም ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲወጡ ይደረጋል።

፲፯.፲፫.፬ የቀረበላቸውን ዋጋቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ የማሻሻል ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች ጥያቄውን መቀበላቸውን እና የመቆያ ጊዜውን ያራዘሙት እስከመቼ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ ማሻሻል ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው።

፲፯.፲፫.፭ በንዑስ አንቀፅ ፲፯.፲፫.፬ በተገለጸው መሠረት የጨረታ ዋስትናውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያላሻሻለ ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል።

## ፲፯.፲፬ የጨረታ ማስከበሪያ

፲፯.፲፬.፩ ከምክር አገልግሎት ግዥ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ግልፅ ወይም ውስን ወይም የሁለት ደረጃ ጨረታ የግዥ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በጨረታው ሠነድ ውስጥ ለእያንዳንዱ ግዥ የሚጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በግልፅ መወሰንና ማመልከት አለባቸው። ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን መ/ቤቱ ካመነበት ለምክር አገልግሎት ግዥም ቢሆን ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያሲዙ ሊጠይቅ ይችላል።

፲፯.፲፬.፪ የመንግስት መ/ቤቱ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.፭ % ያላነሰና ከ፪ % ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ወስኖ በጨረታ

ጥሪው እና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ መግለፅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 500,000.00 የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

፲፮.፲፮.፫ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፮.፪ በተገለጸው መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ማስከበሪያ መጠንን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

ለ/ በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

ሐ/ ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

መ/ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

ሠ/ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በመ/ቤቱ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፣

፲፮.፲፮.፬ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደተጫራቹ ምርጫ በጥሬ ገንዘብ ወይም ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ወይም የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተርኦፍ ክሬዲት ሊሆን ይችላል፡፡

፲፮.፲፮.፭ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፮..፬ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራ ዘርፍ የተሠማሩ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ለጨረታ ማስከበሪያ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የመድን ዋስትና ቢያቀርቡ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፲፮.፲፮.፮ ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ ፳፰ ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፮.፯ የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፮.፰ ማናቸውም ተጫራች የሚከተሉትን ተግባራት ባለመፈጸሙ ምክንያት ያስያዘው ዋስትና በመንግስት መ/ቤቶች ሊወረስበት ይችላል:-

ሀ/ በጨረታ ሠነዱ የተገለጸው የመጫረቻ ሠነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ወይም በመጫረቻ ሠነዱ ላይ በተገለጸው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከጨረታው ካገለለ፣

ለ/ በጨረታው ውድድር አሸናፊ በመሆኑ ውል እንዲፈርም እና የውል ማስከበሪያ እንዲያስዝ ተጠይቆ ውል ለመፈረም እና የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

## ፲፮.፲፯ የመጫረቻ ሠነድ መረከብ

፲፮.፲፯.፩የመንግሥት መ/ቤቶች ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን የሚያስገቡበት የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት አለባቸው:: የጨረታ ሳጥኑም የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለፀው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል::

፲፮.፲፯.፪ የጨረታ ሳጥን ደህንነት የተጠበቀ መሆን ያለበት ሲሆን ጨረታው እስከሚከፈት ድረስ ቁልፉ በግዥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተይዞ መቆየት ይኖርበታል::

፲፮.፲፯.፫ እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም የመጫረቻ ሰነድ ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት:: ሆኖም ለግዥው የሚቀርበው የመጫረቻ ሠነድ በሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ መ/ቤቱ የጨረታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ የመጫረቻ ሠነድ የሚረከብ ሠራተኛ በመመደብ በተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሰነድ መረከብ ይኖርበታል::

፲፮.፲፯.፬ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፯.፫ ላይ በተገለጸው መሰረት የመንግስት መ/ቤቱ ለሚረከበው የመጫረቻ ሰነድ መረከቡን የሚያረጋግጥ የመተማመኛ ሰነድ ሊሰጥ ይገባል:: በዚህ መሰረት የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች ደህንነት መጠበቁን □ፅዬ ሥራ ሂደት ባለቤት ማረጋገጥ ይኖርበታል::

፲፯.፲፯.፮ ከመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ እሽጉ ሳይከፈት ወዲያውኑ ለተጫራቹ ተመላሽ መደረግ አለበት::

## ፲፯.፲፰ □ፊ ረታ አከፋፈት

፲፯.፲፰.፩ ፊ ረታ□ ‹ የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በተገለጸው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በግልጽ ይሆናል:: ጨረታው ሲከፈትም፣

ሀ/ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ይሆናል:: ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኝ መቅረቱ የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፣

ለ/ የጨረታ አከፋፈት ሂደቱን እስካላወከ እና የቦታ ጥበት እስከሌለ ድረስ በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መገኘት የሚፈልግ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው ሰው በታዛቢነት መገኘት ይችላል፣

ሐ/ እስከተቻለ ድረስ የግዥው ተጠቃሚ ከሆኑ ሥራ ሂደቶች የሚወከሉ ባለሙያዎች በአከፋፈት ስነ - ስርዓቱ ላይ ሊገኙ ይችላሉ::

፲፯.፲፰.፪ በአንድ ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ጨረታ ከሆነ መ/ቤቶች እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ያቀረበውን የመጫረቻ ሠነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለውሉ ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነት እና መጠን እና ማናቸውም ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንጻራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያስባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች በንባብ ማሰማት አለባቸው::

፲፯.፲፰.፫ ጨረታው በሁለት ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ:-

ሀ/ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት የቴክኒክ ዶክመንቱን የያዘው ኤንቬሎፕ እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦች በንባብ መሰማት አለባቸው::

ለ/ የሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎፕ ሳይከፈት አንድ ላይ በሌላ አንቬሎፕ ታሽጎና በእሽጉ ላይ የጨረታው መለያ ቁጥር ተፅፎበት፣ የዋጋ ኤንቬሎፖች መሆናቸው ተገልጾ እና ጨረታውን የከፈቱት የመ/ቤቱ ባልደረቦች ተፈራርመውበት ሁለተኛው ዙር የጨረታ መክፈቻ ሥነ - ሥርዓት እስከሚካሄድ ድረስ የታሸገው ፖስታ በግዥ ሥራ ሂደት ወይም በሥራ ሂደቱ ባለቤት በጥንቃቄ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ለሁሉም ተጫራቾች በተመሳሳይ ጊዜ በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል::

መ/ የቴክኒክ ግምገማውን ሳላለፉ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ተጫራቾቹም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ አቤቱታ የሚቀርብበት እና የሚመረመርበት ስርዓት በዚህ መመሪያ ክፍል አሥር የተገለፁትን ሁኔታዎች ተከትሎ ይሆናል፡፡

ሠ/ የቴክኒክ ውጤታቸው ተቀባይነት ላገኘ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ የዋጋ ኤንቨሎፕ የሚከፈትበትን ዕለት፣ ሰዓት እና ቦታ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ደብዳቤውም በዕኩል ጊዜ እንዲደርሳቸው መደረግ እና ሁሉም ፈቃደኛ ተጫራቾች በጨረታው የዋጋ ኤንቬሎፕ መክፈቻ ሥነ - ሥርዓት ላይ እንዲገኙ የሚያስችላቸው በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሆኖም አቤቱታ የቀረበ ከሆነ አቤቱታው ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የዋጋ ኤንቬሎፑ መከፈት የለበትም፡፡

ረ/ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፰.፫ (ሠ) መሠረት የሚደረገውን ጥሪ ተከትለው የቴክኒክ ግምገማውን ያለፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚገኙበት ቀደም
ሲል □ቀረበውና የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ በግልጽ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡

ሰ/ ለዋጋ ውድድር ያለፉ ተወዳዳሪዎችን ኤንቬሎፕ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፰.፫(ረ) ላይ በተገለጸው መሠረት በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለግዥው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለው መጠኑን እና ሁኔታውን፣ እንዲሁም ከዋጋ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት::

ሸ/ በቴክኒክ ውድድር ተቀባይነት ያላገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንዲሁም የዋጋ መወዳደሪያቸውን የያዘው ኤንቬሎፕ ሳይከፈት የቴክኒክ ግምገማ ውጤት እንደታወቀ ለተጫራቾቹ ተመላሽ መደረግ

አለበት፡፡ ሆኖም በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፰.፫ (መ) መሠረት በቴክኒክ ግምገማው ወጠ
ኍት ላይ አቤቱታ □ቀረበ ከሆነ በአቤቱታው ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ወሳኔ እስኪታወቅ ድረስ በቴክኒክ የወደቁት ተጫራቾች የዋጋ ማወዳዳሪያ ኢንቬሎፑም ሆነ ያስያዟቸው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስታና ተመላሽ አይደረጉም ፡፡

፲፮.፲፰.፬ ሀ/ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጨረታውን እንዲከፍቱ የሚመድባቸው አባላት ተጫራቾች ያቀረቡትን ዋናውን የመጫረቻ ሠነድ በጨረታ መክፈቻ ስነ ሥርዓቱ ላይ ከፍተው ለተጫራቾች በንባብ ማሰማት ያላባቸውን መረጃዎች ከሠነዱ ላይ ካነበቡ በኋላ የመጫረቻ ሠነዱ እያንዳንዱ ገጽ ላይ በመፈራረም እንደገና በፖስታ አሸገውና ፖስታው ላይ በመፈራረም የሥራ ሂደቱ ባለቤት ጋር በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ/ ጨረታውን እንዲከፍቱ በመ/ቤቱ የተመደቡት አባላት የጨረታውን አከፋፈት ሂደት የሚያሳይ ቃለ-ጉባዔ መያዝ አለባቸው፡፡ ቃለ-ጉባዔውም የተጫራቾቹን ሥም፣ያቀረቡትን ዋጋ፣የሰጡት የዋጋ ቅናሽ ካለ የዋጋ ቅናሹን፣ያቀረቡትን የጨረታ ማስከበሪያ መጠንና የቀረበበትን ፎርም እና በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ የተነሡ ሌሎችንም አስፈላጊ ነጥቦች የሚይዝ ይሆናል፡፡ ቃለ-ጉባዔው በጨረታ አከፋፈት ሂደቱ ላይ ተመድበው በተገኙት አባላት ይፈረማል፡፡ ጨረታው በተከፈተበት ጊዜ የተገኙ ተጫራቾች መገኘታቸውን በሚያረጋግጠው ዝርዝር ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል፡፡

፲፮.፲፰.፭ ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ የመጫረቻ ሠነድ ለቀጣይ ውድድር ሊያገለግል አይችልም፡፡

፲፮.፲፰.፮ ማናቸውም ተጫራች በጨረታ መክፈቻ ሂደት ወቅት ከጨረታው ውጭ ሊደረግ አይገባም፡፡

## ፲፮.፲፱ ጨረታን መገምገምና ማወዳደር

### ፲፮.፲፱.፩ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ

፲፮.፲፱.፩.፩ የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ለቀጣዩ ዝርዝር የግምገማ ሂደት ሊያሳልፈው የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሠነድ በመክፈቻ ስነ-

ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

፲፮.፲፱.፩.፪ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለበትም፣

ሀ/ በጨረታው የተወዳደረው አቅራቢ መ/ቤቱ የሚፈልገውን አነስተኛውን የጥራት መመዘኛ እና ሌሎች መሰረታዊ መስፈርቶችን ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፱.፩.፫ መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

ሐ/ ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ፣

መ/ በመሥሪያ ቤቱ የተጠየቁትን የጨረታውን ይዘት የሚወስኑ ማስረጃዎች ያላቀረበ ከሆነ፣

ሠ/ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፱.፩.፫ መሠረት በተደረገው የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ/Arithmetic Error / የመጣው ጠቅላላ ዋጋ በጨረታ መክፈቻ ስነ-ሥርዓት ላይ ከተነበበው ጠቅላላ ዋጋ ከ፪% በላይ በሆነ መጠን የሚበልጥ ወይም የሚያንስ ከሆነ፣

፲፮.፲፱.፩.፫ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፱.፩.፩ ላይ የተመለከተው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቱ በምርመራ ወቅት የተገኙ የሒሳብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉትን የማስተካከያ ዕርምጃዎች የመንግስት መሥሪያ ቤቱ ባፋጣኝ ለሚመለከተው ተጫራች በፅሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡ ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ ከጨረታው እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፲፮.፲፱.፩.፬ በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ባህርይዎች፣ የውል ሁኔታዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ነጥቦች ጋር መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታው ቁምነገር ሳይለወጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም የመንግስት መ/ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጎ ሊቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ

በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

## ፲፮.፲፱.፪ ዝርዝር ግምገማ ማድረግና አሸናፊውን መለየት

፲፮.፲፱.፪.፩ የመንግስት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ የተቀበላቸውን የመጫረቻ ሰነዶች እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በጨረታ ሠነዱ ውስጥ ከተገለጸው መስፈርት ውጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በጨረታ ሰነዱ በሚገለጸው መሠረት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ከሚከተሉት የግምገማ ስርዓቶች በአንዱ መጠቀም ይኖርበታል:-

ሀ/ በአንድ ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ መ/ቤቱ የሚፈልገውን አነስተኛ የጥራት ደረጃና ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም

ለ/ በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ መ/ቤቱ ከሚያስቀምጠው አነስተኛ የጥራት ደረጃና ሌሎች መሰረታዊ የሆኑ መስፈርቶች በተጨማሪ የግዥውን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ለቴክኒክና ለፋይ በቅትሚጸ በፊ ረታ ሠነዱ ውስጥ የተሰጠውን የነጥብ ድርሻ መሠረት በማትረፅ በሚካሄድ የቴክኒክና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች በመምረጥ ይሆናል፡፡

ሐ/ በጨረታ አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች የሚመረጠው ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ሀ እና ለ መሠረት ተገምግሞ ቢሆንም ግዥው የግንባታ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ የመ/ቤቱ የጨረታ ገምጋሚ ቲም ወይም የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አሸናፊ የሚሆነውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ ከመምረጡ በፊት ለአሸናፊነት የታጨው ተጫራች ያቀረበው የጨረታ ዋጋ ፡-

፩/ በከፍተኛ ሁኔታ ያልተመጣጠነ መሆኑን ወይም

፪/ በሚሰሩ ስራዎች ላይ ከፍተኛ የነጠላ ዋጋ የቀረበ መሆኑን ወይም

፫/ በቅድሚያ ከተገመተው አጠቃላይ ግምታዊ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ያነሰ ወይም እጅግ የናረ መሆኑን ወይም

፬/ የተሰጠው የዋጋ ተቀናሽ /Rebate/ ከ፲ ከመቶ በላይ መሆኑን ካረጋገጠ ከግንባታ ዘዴዎች እና ከተቀመጠው ፕሮግራም አንፃር የነዚህን ዋጋዎች ውስጣዊ ብቃት ወይም ወጥነት ለማሳየት ሲባል

ዝርዝር የዋጋ ትንተና ለማናቸውም ወይም ለሁሉም የሥራ ዝርዝሮች ተጫራቹ እንዲያቀርብ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

መ/ ከላይ በፊደል ተራ ሐ ላይ በተቀመጠው መሠረት የቀረበው የዋጋ ትንተና ከተገመገመ በኋላ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ የውል ዋጋ ግምት ሠንጠረዦችን ግምት ውስጥ በማስገባት በውሉ መሠረት ሊደርስበት ከሚችለው ከማንኛውም የገንዘብ ኪሳራ ለመጠበቅ ሲባል በተጫራቹ ወጪ የውል ማስከበሪያ ዋስትና የገንዘብ መጠንን ወይም በቅናሽ ወቅት የሚያዝ የመያዣ መጠንን በቂ በሆነ መጠን ከፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአሸናፊነት የታጨው ተጫራች በሁኔታው የሚስማማ መሆኑን በደብዳቤ እንዲገልጽ በመጠየቅ መስማማቱን ከገለፀ ተጫራቹን አሸናፊ አድርጎ መምረጥ፣ የማይስማማ ከሆነ ግን ተጫራቹን ከጨረታ ውጪ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፱.፪.፪ ዝርዝር ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

፲፮.፲፱.፪.፫ እንደአስፈላጊነቱ የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

፲፮.፲፱.፪.፬ ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረታ ዘዴ የሚፈፀም ሆኖ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሠነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የጨረታ ግምገማው ታክስን ማካተት ይኖርበታል፡፡

፲፮.፲፱.፪.፭ በግምገማ ወቅት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭/፫ መሰረት ለሀገር ውስጥ ምርት ወይም አገልግሎት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፲፮.፲፱.፪.፮ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፱.፪.፭ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት መ/ቤቱ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተወሰኑ መስፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፤ ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ፡-

ሀ/ እኩል የሚወጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሦስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለፅ የሚችል መሆን ይኖርበታል፣

ለ/ መስፈርቶቹ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለይ በጨረታ ዝርዝር መግለጫው ላይ መገለፅ ይኖርባቸዋል፣

ሐ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይኸው ተገልፆላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፣

መ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ እስከተቻለ ድረስ እኩል የወጡት ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶ የሰጡ ት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲነበብላቸው ይደረጋል፣

ሠ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ ተገምግሞ የተሻለ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፣

ረ/ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፲፱.፪.፮ ፊደል ተራ "ሠ" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የወጡት ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ መሰረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በእጣ እንዲለይ ይደረጋል::

፲፮.፲፱.፪.፯ የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ የዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ሳይለውጥ እንደአስፈላጊነቱ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ብዛት (መጠን) እስከ ፳% (ሃያ በመቶ) ድረስ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር የሚችል ስለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ላይ መገለጽ ይኖርበታል::

፲፮.፲፱.፪.፰ የመንግስት መ/ቤቶች የማናቸውም ጨረታ ግምገማ በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ለተጫራቾች መግለጽ አለባቸው:: ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ግምገማውን በጊዜው ማጠናቀቅ ካልቻሉ

ተጫራቾች ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ እንዲያሻሽሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፯.፲፰.፩ መሠረት መጠየቅ ይገባቸዋል፡፡

፲፯.፲፱.፪.፱ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መሥሪያ ቤት የቀረበው አንድ ተጫራች ያቀረበው የመወዳደሪያ ሃሳብ አጥጋቢ እና ዋጋውም ተወዳዳሪ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች በጨረታ ሰነድ ላይ ያለመኖራቸውን ካረጋገጠ ድጋሚ ጨረታ ማውጣት ሳያስፈልግ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፲፯.፲፱.፫ ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት

ድጋሚ ጨረታ ማውጣት የሚያስፈልገው፡-

ሀ/ በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ከተገመተው ወጪ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማውጣት የሚሻል መሆኑን ሲያምንበት ወይም፣

ለ/ የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይህን ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተዘረጉትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር (ሁኔታ) መኖሩ ሲረጋገጥ ወይም በጨረታ ሰነዱ ላይ ለውጥ በማድረግ በርካታ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማግኘት የሚቻል መሆኑ ሲታመን፣

## ፲፯.፳ ል□ አስተያየት

፲፯.፳.፩ ከአንድ አቅራቢ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባታ ዘርፍ እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡፡

፲፮.፳.፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳.፩ መሰረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት:: ይኸውም:-

ሀ/ ለመድሐኒት እና የህክምና መሣሪያዎች ግዥ ፳፭% በመቶ (ሃያ አምስት በመቶ)

ለ/ ለሌሎች ዕቃዎች ግዥ ፲፭% በመቶ (አሥራ አምስት በመቶ)

ሐ/ ለግንባታ ሥራና ለምክር አገልግሎት ግዥዎች ፯.፭% (ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ)

፲፮.፳.፫ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳.፪ (ሀ እና ለ) መሠረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድሐኒቱን ወይም የህክምና መሣሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጪ ፴፭% (ሰላሳ አምስት በመቶ) እና ከዚህ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም '' የታከለ ዋጋ'' ማለት፣ ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም፡፡

፲፮.፳.፬ ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳.፪(ሐ) መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል:-

ሀ/ ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

ለ/ ከኩባንያው አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ፶% (ሃምሳ በመቶ) በላይ በኢትዮጵያውያን የተያዘ ከሆነ፣

ሐ/ ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ፶% (ሃምሳ በመቶ) በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

መ/ ከኩባንያው ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ ፶% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

፲፮.፳.፫ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪን የገበያ ዕድል ለማስፋፋትና ለማበረታታት አሻሽሎ ባወጣው ደንብ ቁጥር ፺፳/፪፻፬ ከአንቀጽ ፺-፲፪ በተዘረዘረው መሠረት ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል ፣

፲፮.፳.፮ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፲፮/፳/፫ የተደነገገው □እንደተጠበቀ ሆኖ መ/ቤቶች የሚያወጡት ፌ ረታ እነዚህን ተቋማት የሚጋብዝ ቢሆንም የሚከተሉት የግዥ አፈፃፀሞች የግዥ አዋጁንና ይህን መመሪያ የተከተለ መሆን ይኖርበታል::

## ፲፮.፳፩ ከጨረታ ውጪ ማድረግ፣

ከሚከተሉት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈፀመን ተጫራች የመንግስት መ/ቤቱ ከጨረታው ውጪ ሊያደርገው ይችላል:-

ሀ/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት አገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት ከሆነ ወይም፣

ለ/ በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ ሀገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ከሆነ፣

ሐ/ □ክልሉን □ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና ይህን መመሪያ የሚጥሱ ድርጊቶችን መፈፀሙ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ/ ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች የገባውን የግዥ ውል ግዴታ ባለማክበሩ በመንግስት ጨረታዎች እንዳይሳተፍ በክልሉ ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ በ□ጻ ራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲሁም በሌሎች ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የግዥና ንብረት አስተዳደር መ/ቤቶች የታገደ ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ የተለየ አስተያየትን ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማናቸውም ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም የመደለያ ሀሳብ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣ ወይም

ረ/ ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ፣ ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ ሲረጋገጥ፣

## ፲፮.፳፪ ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት

፲፮.፳፪.፩ በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከተጫራቾች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል፡፡ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ/ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት፣ ወይም

ለ/ የሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካትታቸው የግዢ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣

፲፮.፳፪.፪ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፪.፩ በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሃሳቡን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋን ወይም ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ መጠየቅ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

## ፲፮.፳፫ ጨረታን ማፅደቅ

፲፮.፳፫.፩ በመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው የግዥ ዳይሬክቶሬት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ጊ□ያዊ ቡድን በተጫራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማፅደቅ ስልጣን ለተሠጠው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

፲፮.፳፫.፪ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሠነዱ በተገለጸው መሥፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈጻጸሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣

፲፮.፳፫.፫ ግዥውን የሚያፀድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው አካል ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

፲፯.፳፫.፬ በንዑስ አንቀጽ ፲፯..፳፫.፪ ላይ በተገለጸው መሰረት ግዥውን የሚያፀድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው አካል እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን ገምጋሚ አካሉም ከአፅዳቂው አካል በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፲፯.፳፫.፭ በአንቀጽ ፲፯.፳፫.፬ ላይ የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ አካሉ ወይም ማንኛውም የጨረታ ገምጋሚ አካል አባል የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሀሣብ ተገልፆ የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

## ፲፯.፳፬. የጨረታ አሸናፊን ማሳወቅ

፲፯.፳፬.፩ የመንግስት መ/ቤቶች የጨረታውን ውጤት በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ለሁሉም ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በ□ሁፍ መግለጽ አለባቸው፡፡ ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለፀው የተሸነፉበትን ምክንያት እና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

፲፯.፳፬.፪ በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚላከው ደብዳቤ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ እና በተጫራቹ መካከል ውል ሊኖር የሚችለው ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በመ/ቤቱ □በላጁ ኃላፊና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

፲፯.፳፬.፫ ተጫራቹ ውል እንዲፈርም የሚላክለት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሀሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ/ ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

ሐ/ ተጫራቹ ማስያዝ የሚገባውን የውል ማስከበሪያ መጠን እና የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን፣

፲፮.፳፬.፬ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ የመንግስት መ/ቤቱ በቅድሚያ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች አሸናፊ በነበረው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ ወይም ለመስራት ፈቃደኛ መሆኑን መጠየቅ፣ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ አሸናፊ በነበረው ተጫራች ዋጋና ሁለተኛ በወጣው ተጫራች ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ከ፭% /አምስት በመቶ/ በላይ ካልሆነ ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች ግዥውን መፈፀም የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በመገምገም በውድድሩ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ግዥውን መፈፀም ካልሆነም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይገባዋል፡፡

፲፮.፳፬.፭ የመንግስት መ/ቤቱ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፬.፩ መሰረት ለተጫራቾች ውጤታቸውን የገለፀ ቢሆንም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ለተወዳዳሪዎች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናቸውን ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራቹ ጋር ውል ፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ፣

## ፲፮.፳፭ የውል ማስከበሪያ

፲፮.፳፭.፩ ከኪራይ አገልግሎት ግዥ በስተቀር ለማናቸውም ሌላ የግዥ ውል የመንግስት መ/ቤቱ የውል ማስከበሪያ መቀበል አለበት፡፡

፲፮.፳፭.፪ ሀ. የጨረታው አሸናፊ ከመ/ቤቱ ጋር ውል ለመ□ራረም ሲቀርብ ለጨረታ ማስከበሪያ ተቀባይነት እንዳላቸው በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፲፮.፬ በተገለፁት የዋስትና ዓይነቶች መሠረት ክፍያ በሚፈፀምበት የገንዘብ ዓይነት ቢያንስ የውሉን ዋጋ ፲% (አስር በመቶ) በውል ማስከበሪያነት ለመንግስት መስሪያ ቤቱ ማስያዝ አለበት፡፡

ለ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ሀ መሠረት መ/ቤቱ አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ተጫራቹ ለውል ማስከበሪያነት ያቀረበውን ዋስትና ትክክለኛነት ዋስትናውን ከሰጠው ባንክ ጠይቆ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፣

፲፮.፳፭.፫ የመንግስት መ/ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን ሲያረጋገጥ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳፭.፪ መሠረት አቅራቢው ያስያዘውን የውል ማስከበሪያ ሙሉ በሙሉ መውረስ ይኖርበታል።

፲፮.፳፭.፬ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፭.፫ የተገለጸው ቢኖርም በአቅራቢው ያልተሟላው የውል ግዴታ በመ/ቤቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ወይም ተጨማሪ ወጪ እንደማያስከትል እና በአቅራቢው ቸልተኝነት ምክንያት የተፈፀመ አለመሆኑ በመ/ቤቱ የግዥ አጽዳቂ አካል ሲታመንበት የውል ማስከበሪያው ለአቅራቢው ሊመልስለት ይችላል።

፲፮.፳፭.፭ የመንግስት መ/ቤቱ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳፭.፬ መሰረት ለወሰዳቸው እርምጃዎች የተሟላ ሰነድ በመያዝ በኤጀንሲው ወይንም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል ሲጠየቅ ማቅረብ እና የአሰራሩን አግባብነት ማስረዳት ይኖርበታል።

፲፮.፳፭.፮ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፭.፪ የተመለከተው ቢኖርም:-

ሀ/ ከአገር ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ተቋራጮች ወይም መድሐኒት እና የህክምና መሣሪያዎች አምራች ድርጅቶች ለሚፈጸም ግዥ ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሠማሩ አማካሪዎች በሚሰጡት የምክር አገልግሎት ሂደት ውስጥ በመ/ቤቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ሲገመት የባለሙያ የካሣ መድን እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይቻላል፣

ሐ/ የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡትን ገንዘብ በውል ማስከበሪያነት ለመጠቀም ይችላሉ። ሆኖም በዚህ መንገድ ለሚያስይዙት ዋስትና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው ስለመሆኑ ከባንኩ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

፲፮.፳፭.፯ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ ይኖርበታል።

## ፲፮.፳፮ የቅድሚያ ክፍያ

፲፮.፳፮.፩ በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ ፴% (ሠላሣ በመቶ) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለፅ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፳፮.፪ ሀ. አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ ቼክ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ሀ መሠረት መ/ቤቱ ቅድመ ክፍያውን ለአቅራቢው ከመክፈሉ በፊት አቅራቢው ለቅድመ ክፍያው ያቀረበውን የቅድመ ክፍያ ዋስትና ትክክለኛነት ዋስትናውን ከሰጠው ባንክ ጠይቆ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፣

፲፮.፳፮.፫ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፮.፪ ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እና የመድሀኒት እና ሕክምና መሳሪያዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፲፮.፳፮.፬ ለአገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መ/ቤቱ በጋራ በሚንቀሳቀስ የባንክ ሒሳብ ገንዘቡን ተቀማጭ በማድረግ ከውሉ ጋር ለተገናኙ እና አስፈላጊ ለሆኑ ወጪዎች በጋራ ፊርማ እንዲከፈል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፲፮.፳፮.፭ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፮.፫ እና ፲፮.፳፮.፬ መሰረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሰረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና የመድን ድርጅት ሲሆን ወይም በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፮.፬ መሰረት ለጥቃቅን ና አነስተኛ ተቋማት የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ከሆነ ውል ሰጪው የመንግሥት መ/ቤት ውል ተቀባይ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ወይም ጥቃቅን ና አነስተኛ ተቋም ጋር የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለበት፡፡ ውሉም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ በውሉ መሠረት ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሙ የሚፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሙ ስም በሚከፈት የተለየ የባንክ ሂሣብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" መሠረት በተከፈተው ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው በውል ሰጪ እና በውል ተቀባዩ የጣምራ ፊርማ እንደሚሆን፣

ሐ/ በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ወይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሙ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን፣

መ/ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ ፶% (ሃምሳ በመቶ) እንዲሁም ለሕንጻ ሥራ የአገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ ፴% (ሰላሳ በመቶ) ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን፣ የሚገልጹ አንቀጾችን ሊይዝ ይችላል::

፲፮.፳፮.፮ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፮.፫(መ) በተመለከተው መሠረት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቅድ ይችላል:-

ሀ/ የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት የማያውል እና በማናቸውም መልክ ለሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካቀረበ፣

ለ/ የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሠሪው መ/ቤት ተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሣሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

ሐ/ መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ የማይንቀሳቀሱ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው::

፲፮.፳፮.፯ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚከፈል ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እንዲሁም ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር ፬ ላይ የተመለከቱት ብቻ ናቸው::

፲፮.፳፮.፰ □ሥራ ተቋራጩ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፮.፮ በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የገዛቸውን መሣሪያዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ ካላጓጓዘ በውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈፀምለትም፡፡

፲፮.፳፮.፱ □ሥራ ተቋራጩ ወይም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሙ የወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው ከሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ወይም በየደረጃው ከሚፈፀሙ አቅርቦቶች ሂሣብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

## ፲፮.፳፯ ውል መፈረም

፲፮.፳፯.፩ ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም አለበት፡፡

፲፮.፳፯.፪ በመንግሥት መ/ቤቱ እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተፈረመ በስተቀር የጨረታው አሸናፊ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም፡፡

፲፮.፳፯.፫ በአቅራቢው እና በመንግስት መሥሪያ ቤቱ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልፅ ማመልከት ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ በውሉ የሚቀርበው እቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ስራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

ለ/ ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፤ ኢንሹራንስ፤ ትራንዚት እና የመሳሰሉ ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆኑ መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈፅማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፣

ሐ/ አቅራቢው በመጫረቻ ሠነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፣

መ/ በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ ወይም በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

ረ/ የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና የተፈፃሚነት ቅድመ ወሰን፣

ሰ/ ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፣

ሸ/ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፣ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ፤

፲፮.፳፪.፬ በንዑስ አንቀፅ ፲፮.፳፪.፫(ሸ) መሰረት የሚወሰደው እርምጃ በሚከተለው መሰረት መሆን ይኖርበታል:-

ሀ/ አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 0.፩% ወይም ፩/፲ሺ የጉዳት ካሳ እንደሚከፍል፣

ለ/ በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ ፲% የሚበልጥ መሆን እንደሌለበት፣

ሐ/ የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ የመንግስት መ/ቤቱ የመቀጫው መጠን ፲% እስከሚሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል የሚገልፅ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ መደረግ አለበት።

፲፮.፳፪.፭ የመንግስት መ/ቤቱ በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በመ/ቤቱ ደረጃ ሊከናወኑ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም።

፲፮.፳፪.፮ በንዑስ አንቀጽ ፲፮.፳፪.፪ ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል።

፲፮.፳፯.፯ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መስሪያቤት የጨረታውን ወይም የቅሬታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለፀበት ቀን ጀምሮ ፯ የሥራ ቀን ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈረም የለበትም::

# ክፍል ፭

## የዓለም አቀፍ ግዥ አፈጻጸም

## ፲፯. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ

፲፯.፩ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ ፶፱ እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፯ ላይ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል::

፲፯.፪ በአዋጁ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተመለከቱት ሌሎች የግዥ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዓለም አቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈፀም የሚችለው ለፅ ዴ□ □ሚ□ለ□ የገንዘብ መጠን ከሚከተለው በላይ ሲሆን ነው፣

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 150,000,000.00 በላይ፣

ለ/ ለዕቃ ግዥ ከብር 50,000,000.00 በላይ፣

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ከብር 7,500,000.00 በላይ፣

መ/ ለአገልግሎቶች ከብር 21,000,000.00 በላይ፣

፲፯.፫ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈፀም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በመሥሪያ ቤቶች ሲጠየቁ ከአምራቹ የተሰጣቸውን ውክልና ማቅረብ አለባቸው::

፲፯.፬ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከተገለጸው ዝርዝር የግዥ አፈጻጸም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተተ አለበት:-

ሀ/ የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዱ የሚዘጋጀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት፣

ለ/ የጨረታው ጥሪ በቂ የሥርጭት ሽፋን ያለውና የውጭ ተጫራቾችን ለውድድር ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ መውጣት ያለበት ሲሆን፣ በተጨማሪም በርካታ

ተጫራቾችን ለማግኘት እንዲቻል የጨረታውን ጥሪ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ ማ□ጣት እና ለተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎች ማሳወቅ ይቻላል፡፡

ሐ/ ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሠነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮.፱ ላይ በተገለጸው መሠረት በቂ ጊዜ መሠጠት አለበት፣

መ/ የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃን ያሟላና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፣

ሠ/ የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋና የጨረታ ማስከበሪያ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በአለም አቀፍ ንግድ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት ሊሆን ይገባል፡፡

ረ/ የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት አሸናፊው የውጭ አገር ተጫራች ከአገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባውን መጠን በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

ሰ/ በአለም አቀፍ ግዥ የሚፈፀሙ ውሎች አዋጁን እና የአፈፃፀም ድንጋጌዎችን እስካልተቃረኑ ድረስ በአለም አቀፍ ንግድ የሚሰራባቸውን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ተመርኩዘው መፈፀም አለባቸው፣

ሸ/ በውሉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ ሊዳኙ ይገባል፡፡

## ፲፰. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

፲፰.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፶፱ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት የውጭ ኩባንያዎች ካልተሳተፉበት በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመን በአዋጁና በዚህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት መ/ቤቶች የሁለት ደረጃን፣ የመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያን፣ የውስን ጨረታንና ከአንድ አቅራቢ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም ዓቀፍ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፡፡

፲፰.፪ በንዑስ አንቀፅ ፲፰.፩ ላይ በተገለፀው መሰረት ከአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች በመጠቀም አለም አቀፍ ግዥ መፈፀም የሚቻለው ለየግዥ ዘዴው የተመለከተውን ሁኔታ እና የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

## ፲፱. በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ

፲፱.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፶፯ እና ፶፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፯ እንደግዥው ዓይነት ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሥርዓት ይከተላል፡፡

፲፱.፪ በንዑስ አንቀፅ ፲፱.፩ የተመለከተው ቢኖርም ለሁለት ደረጃ ጨረታ የሚደረገው የጨረታ አፈፃፀም የሚከተሉትን ልዩ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል’

፲፱.፪.፩ በጨረታ ጥሪው ላይ ግዥው በሁለት ደረጃ ጨረታ የሚፈፀም መሆኑ መገለፅ ይኖርበታል፣

፲፱.፪.፪ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ አይጠየቁም፣

፲፱.፪.፫ በመጀመሪያ ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የመንግስት መ/ቤቱን አጠቃላይ ፍላጎት የሚገልፅ ሆኖ አላማው ከዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ሐሳቦች መሠረት ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት ስለሆነ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ መጠይቆችን እና መግለጫዎችን ማካተት ይኖርበታል፣

፲፱.፪.፬ በመጀመሪያው ዙር ጨረታ ላይ የተጫራቾች መገኘት ሳያስፈልግ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበው የቴክኒክ ሐሳብ ማቅረቢያ ሰነድ በጨረታ ጥሪው በተገለፀው ሁኔታ እንዲከፈት ይደረጋል፣

፲፱.፪.፭ በንዑስ አንቀጽ ፲፱.፪.፫ መሰረት የሚከናወነው ግምገማ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሐሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም:-

ሀ/ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር የመንግስት መ/ቤቱ ውይይት ሊያደርግ ይችላል፣

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት እጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፣

፲፱.፪.፮ በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ እስከተቻለ ድረስ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፮ እና ፲፯ለግልፅ ጨረታ የተገለፀውን አሠራር መከተል ይኖርበታል።

፲፱.፪.፯ በንዑስ አንቀፅ ፲፱.፪.፮ ላይ በተገለፀው መሰረት በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሁለተኛው ዙር ውድድር እንዲሳተፉ ጥሪ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡም ይደረጋል።

፲፱.፪.፰ መ/ቤቱ ለሁለተኛው ዙር የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መላክ ወይንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው እንዲወስዱ ማድረግ ይኖርበታል።

፲፱.፪.፱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፲፱.፪.፯ ላይ በተገለፀው መሰረት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን ለመውሰድ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል።

# ፳. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ

፳.፩ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባሕርይ አንፃር በቅድሚያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት መሠረት በማድረግ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደግዥው አይነት ብሔራዊ ወይም ዓለም □ቀፍ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል።

፳.፪ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል

ሀ/ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህርይው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፤ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ፣ የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም

ለ/ የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሣሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም

ሐ/ የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጥ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው፣

፰.፫ ጨረታው የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ በማስታወቂያው ላይ መገለፅ ይኖርበታል።

፰.፬ የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ የቅድመ ብቃት ጨረታ ለመፈጸም በኤጀንሲው የተዘጋጀውን የቅድመ ብቃት ጨረታ መደበኛ የጨረታ ሠነድ መሠረት በማድረግ ይሆናል ። የቅድመ ብቃት መምረጫ መሥፈርት እንደግዥው ባህርይና ዓይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት ማስረጃ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል ።

ሀ/ በተመሳሳይ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

ለ/ ድርጅቱ ሥራውን ለማከናወን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል ተመጣጣኝ የሰው ኃይል፣ ማሽነሪ፣ የማምረቻ መሣሪያ ብዛት እና የተሟላ ኢንፍራስትራክቸር ያለው መሆኑን፣

ሐ/ ድርጅቱ አሁን በመሥራት ላይ ያለውን የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት ወይም መጠን፣

መ/ ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን፣

፰.፭ የተጫራቾች ግምገማ የሚከናወነው ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በመንግስት መ/ቤቱ የተዘጋጀውን መሥፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፰.፮ ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መሥፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት።

፰.፯ የመንግስት መ/ቤቶች በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንዲችሉ ሊፈቅዱ ይችላሉ።። ሆኖም የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥው ሂደት የሚኖራቸውን ውድድር እንደማያጠብ በመ/ቤቱ

ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሠነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም::

፳.፰ በንዑስ አንቀጽ ፳.፮ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሰረት በማድረግ በተካሄደ ግምገማ ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በጨረታው በግል እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም::

፳.፱ የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በመ/ቤቱ ተቀባይነት እንዳገኘ ውጤቱ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች በእኩል ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል::

፳.፲ አንድ ተጫራች በጨረታው ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም ለቅድመ ብቃት ውድድር የሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ የመንግስት መ/ቤቱ ድርጅቱ ውሉን እንዲፈርም ላይፈቅድ ይችላል::

፳.፲፩ በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተመለከተውን ስርአት በመከተል የሚዘጋጀው የጨረታ ሠነድ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድሩ ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በየአድራሻቸው እንዲላክላቸው ወይም ከመ/ቤቱ ቀርበው እንዲወስዱ የሚደረግ ሲሆን፣ ቀሪው የግዥ አፈፃፀም ስርአት በዚህ መመሪያ የተደነገገውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል::

## ፳፩. በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

፳፩.፩ የመንግስት መ/ቤት የምክር አገልግሎት ግዥን የመወዳደሪያ ሀሣብ በመጠየቅ መፈፀም የሚኖርበት ሲሆን የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር ፱፻ሺህ (ዘጠኝ መቶ ሺህ) በላይ በሚሆንበት ጊዜ የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፳፪ መሰረት ማካሄድ ይኖርበታል::

፳፩.፪ የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች አመራረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይፈፀማል፤

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፳፪ መሰረት በወጣው የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጥሪ መሠረት በመምረጥ፣

ለ/ የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማካሪዎች ውስን ሲሆኑ እነዚህን አማካሪዎች በሙሉ በመጋበዝ፣

ሐ/ የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር ፱፻ሺህ (ዘጠኝ መቶ ሺህ) በታች ሲሆን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ በመምረጥ፣

፳፩.፫ የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች ቁጥር እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሰ እና ከሰባት ያልበለጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

፳፩.፬ መ/ቤቱ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች የጥሪ ደብዳቤ በተመሳሳይ ጊዜ በአድራሻቸው መላክ አለበት፡፡ ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ መ/ቤቱ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን ሊልክላቸው ይችላል፡፡

፳፩.፭ ለመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ኤጀንሲው ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም እንዲሁም በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተቀመጠውን ስርአት በመከተል የሚዘጋጅ መሆን ይኖርበታል፡፡

፳፩.፮ የመንግስት መ/ቤቱ ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፤ ስለአሰራር ዘዴው፤ በስራው ስለሚሰማራው የሰው ኃይል እና መሳሪያ፤ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል ፡፡

፳፩.፯ በንዑስ አንቀፅ ፳፩.፮ መሰረት የሚደረገው ስምምነት የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያሰጠው መሆን የለበትም፡፡

፳፩.፰ በንዑስ አንቀጽ ፳፩.፱ ስር የተገለጹት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ ስር የተገለጹትን የግልጽ ጨረታ አሠራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡

፷፩.፱ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፷፩(፲፣ ፲፩፣ ፲፪፣ ፲፫፣ ፲፬ እና ፲፭) በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቬሎፕ ታሽጎ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ለምክር አገልግሎቱ የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ የሚከተለውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

## ፷፩.፲ በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

፷፩.፲.፩ የመንግስት መ/ቤቶች ለምክር አገልግሎት የጨረታ ሠነድ በሚያዘጋጁበት፣ በዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርበውን እያንዳንዱን የቴክኒክ ሃሳብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ ከሚሰጠው ሥራ ጋር በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣

ለ/ በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣

ሐ/ ምክሩ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ የሚያስገኘውን ዕውቀት፣

መ/ የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሐሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጎች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ፣

፷፩.፲.፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፷፩.፲.፩ ላይ ለተመለከቱት መስፈርቶች መ/ቤቱ እንደሚገዛው የምክር አገልግሎት ዓይነት ለእያንዳንዱ መስፈርት ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ነጥብ መስጠት ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የአማካሪው ልዩ ልምድ .......................... ከ፭ እስከ ፲ ነጥብ

ለ/ ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው
የምክር ዘዴ ............................................ ከ፳ እስከ ፶ ነጥብ

ሐ/ ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ ...................... ከ፭ እስከ ፲ ነጥብ

መ/ በምክር አገልግሎቱ ለሚሳተፉ ቁልፍ
ባለሙያዎች…...............................................ከ፴ እስከ ፳ ነጥብ

ሠ/ የኢትዮጵያውን ተሳትፎ ........................... ከ፭ እስከ ፲ ነጥብ

፳፩.፲.፫ በቴክኒክ ብቃት ፸% (ከመቶ ሰባ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው ፸% እና ከዚህ ነጥብ በላይ ያገኙት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት ይከፈታል፡፡

፳፩.፲.፬ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት፡፡

፳፩.፲.፭ የምክር አገልግሎቱ የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስን ይጨምራል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የመጓጓዣ፣ የትርጉም፣ የጽሕፈት ሥራ ወጪን እና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡

፳፩.፲.፮ ዝቅተኛ የመጫረቻ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ ፻ (አንድ መቶ) ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን፣ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ግን እንዳቀረቡት ዋጋ ከፍተኛ ላቀረበው አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል፡፡

፳፩.፲.፯ የቴክኒክ ግምገማ ፹% /ሰማንያ በመቶ/ የነጥብ ድርሻ፣ የዋጋ ግምገማ የነጥብ ድርሻ ደግሞ ፳% (ሃያ በመቶ) ይሆናል፡፡

፳፩.፲.፰ ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

፳፩.፲.፱ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ የተገለጸውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ፳፩.፲፩ በሚከናወነው የሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

፳፩.፲፩.፩ በሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል:-

ሀ/ የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለየ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሠነድ ወይም ቢጋር ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣

ለ/ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዩች፣

ሐ/ የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፣

፳፩.፲፩.፪ የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል::

፳፩.፲፩.፫ በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል

፳፩.፲፩.፬ በንዑስ አንቀጽ ፳፩.፲፩.፫ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም በላይ ከሆነና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል::

፳፩.፲፩.፭ በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የውል ስምምነት እንደተፈረመ የሌሎች ተወዳዳሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾቹ ተመላሽ መደረግ አለበት::

## ፳፩.፲፪ በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ፣

ሀ/ በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው::

ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮.፲፰.፫ "ሀ" መሠረት የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል::

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማው በንዑስ አንቀጽ ፳፩.፲.፩፣ ፳፩.፲.፪ ፳፩.፲.፫ እና ፳፩.፲.፬ ላይ የተመለከቱት ሥርዓቶች ተከትሎ የሚፈጸም ይሆናል::

መ/ በቴክኒክ ግምገማው ተፈላጊውን መስፈርት ያሟሉት ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል:: ለጨረታው በእያንዳንዱ ተጫራች የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት::

ሠ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል::

ረ/ ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና ከፍተኛ የቴክኒክ ውጤት ያለው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል::

## ፳፩.፲፫ በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

፳፩.፲፫.፩ በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው::

፳፩.፲፫.፪ መ/ቤቶች በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾችን ለመገምገም ሲፈልጉ ዝቅተኛውን የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ መጠን በመወሰን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ ይህንኑ ነጥብ በግልጽ ማመልከት አለባቸው::

፳፩.፲፫.፫ የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል::

፳፩.፲፫.፬ በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል::

፳፩.፲፫.፭ በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት::

፳፩.፲፫.፮ በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ውድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል:: ለጨረታው በተጫራቾች የቀረበው ዋጋ በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት::

፳፩.፲፫.፯ በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ካሟሉት ተወዳዳሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሠጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል::

## ፳፩.፲፬ በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ፣

ሀ/ በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠ ን ሲሆን ነው::

ለ/ ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር ፶ ሺህ የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው::

ሐ/ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚዘጋጀው ማጣቀሻ/ቢጋር/ አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ መሆን አለበት::

መ/ ከአቅራቢዎች ዝርዝር ወይም መ/ቤቱ ያለውን መረጃ በመጠቀም በውድድሩ እንዲሳተፉ ከመረጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሐሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስበት ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::

## ፳፩.፲፭ አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ፣

የመንግሥት መ/ቤቶች የምክር አገልግሎት ግዥን ከአንድ አማካሪ ለመፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ እና ፶፪ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፩ የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው:::

## ፳፪. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

፳፪.፩ የመንግስት መ/ቤት የሚገዛው የምክር አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ ከብር ፱፻ ሺህ /ዘጠኝ መቶ ሺህ/ የሚበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ ጥሪ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ/ ለፍላጎት መግለጫ የሚደረገው ጥሪ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፯.፪ ወይም ፲፯.፬ (ሀ) እና (ለ) ላይ የተመለከተውን ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን በተጨማሪነት ጥሪው የተደረገው ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ፍላጎታቸውን እንዲገልፁ መሆኑን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ጥሪው የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት አይነት፣ የሚጠበቀውን ውጤት ፣ ጊዜውን፣ አማካሪው ሊኖረው የሚገባውን ብቃት፣ የስራ ልምድ እና የመሳሰሉትን የያዘ እና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን መረጃ ዝርዝር እና የሚያቀርቡበትን ቦታና ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት፣

ሐ/ ፍላጎታቸውን ያሳወቁ ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት መረጃ ተገምግሞ የተፈለገውን የምክር አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ብቃት ያላቸው በቅደም ተከተላቸው መሠረት እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሱ እና ከሰባት ያልበለጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመርጠው በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፳፩ መሰረት የመወዳደሪያ ሐሳባቸውን እንዲያቀርቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## ፳፫. የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም፣

የአዋጁ አንቀጽ ፵፱ እና ፶ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

፳፫.፩ በአዋጁ አንቀጽ ፵፱.፩ መሠረት በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፯ ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ጨረታ የተፈቀደውን ዝርዝር የአፈጻጸም ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፳፫.፪ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፤

፳፫.፪.፩ የጨረታ ጥሪው በቀጥታ ለዕጩ ተወዳዳሪው በአድራሻው የሚላክ ሆኖ::

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ ይኖርበታል::

ለ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም ግዥው በንዑስ አንቀፅ ፳፫.፫ በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ገደብ ውስጥ ከሆነ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ ይኖርባቸዋል::

፳፫.፪.፪ የመንግስት መ/ቤቱ በውስን ጨረታ የተጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም::

፳፫.፪.፫ በውስን ጨረታ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሠነዳቸውን ካቀረቡ የጊዜ ገደቡ እስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ የመንግስት መ/ቤቱ አዲሱን የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ለሁሉም ተጫራቾች በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረታው እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል::

፳፫.፪.፬ የመንግሥት መ/ቤቱ ለግዥው ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መጠየቅ አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን አያይዞ ሊልክ ይችላል::

፳፫.፪.፭ መ/ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ ፶(፩)መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ ቁጥራቸው ውስን የሆኑትን ተጫራቾች በጨረታው ውድድር እንዳይሳተፉ ያደርጋል ብሎ ሲያምን የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ዕጩ ተጫራቾች በዚህ መመሪያ አባሪ ቁዓ ር ፳ የተመለከተውን የስምምነት ማረጋገጫ ፎርመው ከመጫረቻ ሠነዳቸው ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል::

፳፫.፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፳፫.፪ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በአዋጁ አንቀፅ ፵፱.፪ መሰረት በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው የሚገዛው ዕቃ፣ የምክር

አገልግሎት፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም አገልግሎት ጠቅላላ ዋጋ ከሚከተለው የማይበልጥ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ.... ከብር 6,000,000.00

ለ/ ለዕቃ ግዥ ......................... ከብር 1,500,000.00

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ...... ከብር 900,000.00

መ/ ለአገልግሎት ግዥ................ ከብር 1,200,000.00

፷፫.፬ በአዋጁ አንቀጽ ፵፱.፫ በተገለጸው መሠረት ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅደም ተከተል መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:-

ሀ/ ግዥውን ለመፈጸም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ በወጣ ጨረታ የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑን፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታ ጥሪውን፤ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና አይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድቡ ሁኔታዎች በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያው እና ሰነዱ ውስጥ አለመኖራቸውን ማረጋገጥ ፣

ሐ/ የመንግስት መ/ቤቱ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ግዥው ቢጋበዙ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማመን፣

መ/ እስከተቻለ ድረስ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በግልፅ ጨረታ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት በማጣራት ምክንያታቸው፤ ሕጋዊ እና የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም ለመጉዳት ያለመ አለመሆኑን፤

፷፫.፭ በግዥ አዋጁ አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ ወይም ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ ወይም ንዑስ አንቀጽ ፫ ላይ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ ከተሟላ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈፀም ይቻላል፡፡

፷፫.፮ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ የሚፈፀመው በግዥ አዋጁ አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ንዑስ አንቀጽ ፫ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ከሆነ ለውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ መጠበቅ ሳያስፈልግ ግዥውን በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም ይቻላል፡፡

፳፫.፯ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፳፫.፩፣ ፳፫.፪፣ ፳፫.፫ እና ፳፫.፬ ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ ላይ የተመለከተውን የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የአፈፃፀም ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

፳፫.፰ በመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚፈፀመው የውስን ጨረታ የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፳፩ ላይ የተገለጹትን ተጨማሪ አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

## ፳፬. በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ የሚፈጸም ግዥ

፳፬.፩ የአዋጁ አንቀጽ ፶፫ እና ፶፮ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ ፳፬.፪ በተመለከተው የገንዘብ ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ የግዥ ዘዴ ለመፈፀም ይችላሉ፡፡

፳፬.፪ የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ የግዥ ዘዴ በየግዥ ዓይነቱ በአንድ ጊዜ በሚፈፀም ግዥና በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ በየግዥ ዓይነቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚ□ናመ□ ዕዴ የሚውለው የገንዘብ መጠን በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፳፬.፪ ከተመለከተው የማይበልጥ ሲሆን በተጫራቾች የቀረቡ የመጫረቻ ሰነዶች በግዥ ባለሙያዎች እንዲገመገም እና በዕዴ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክትር እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፣

| የግዥው ዓይነት | በአንድ ጊዜ ለግዥ አይነቱ የሚውለው የገንዘብ መጠን | በአንድ በጀት አመት በተመሣሣይሁኔታ ለሚፈጸም ግዥ የሚውለው የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|
| የግንባታ ሥራ ግዥ | እስከ ብር 300,000 | እስከ ብር 900,000 |
| የዕቃ ግዥ | እስከ ብር 225,000 | እስከ ብር 750,000 |
| የምክር አገልግሎት ግዥ | እስከ ብር 60,000 | እስከ ብር 180,000 |
| የሌሎች አገልግሎት ግዥ | እስከ ብር 150,000 | እስከ ብር 450,000 |

፳፬.፫ የመንግስት መ/ቤቱ በአካባቢ ማስታወቂያ በተመለጠፍ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈጸም በውድድሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚመርጣቸው እጩ ተወዳዳሪዎች መ/ቤቱ የሚፈልገውን

ዝቅተኛ የጥራት መስፈረት ያማሉ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር በመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ፣የዘመኑን የንግድ ፈቃድ እድሣት ያከናወኑ እና ሌሎች መ/ቤቱ ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ መስፈርቶች ያማሉ ሆነው እስከተቻለ ድረስ ውድድሩ ፍትሀዊ እንዲሆን ቢያንስ እስከ 3 አቅራቢዎችን ማወዳደር ይኖርበታል፣

፳፬.፬ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፳፬.፫ የተገለፀው ቢኖርም የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም አንዴ ማስታወቂያ አውጥተው በቂ ተጫራች ባይቀርብም የመጫረቻ ሰነዳቸውን ባስገቡት ተጫራቾች የቀረበው ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ እስከቻሉ ድረስ የተገኙትን ተጫራቾች አወዳድረው ወይም የተገኘው ተጫራች አንድ ከሆነም ከዚያው ተጫራች ግዥ መፈፀም ይችላሉ፣

፳፬.፭ እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሆኖ ያቀረበውን ዋጋም መለወጥ አይፈቀድለትም፡፡ ዕጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በመንግስት መ/ቤቱ እና በዕጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም፡፡

፳፬.፮ የመንግስት መ/ቤቱ ከፍተኛ የዋፉ ልዩነት ሊያመጡ የሚችሉ የጥራት ደረጃ- ችን በመለየት በዋጋ የሚወዳደሩት ተመሣሣይ የጥራት ደረጃ ያላቸው አቅርቦቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፣የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በመ/ቤቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጐ መምረጥ አለበት፣

፳፬.፯ በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለሚፈጸም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር ተመሣሣይ ይዘት ባለው ስሌት የተገኘ እና ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፣

፳፬.፰ መ/ቤቱ በአካባቢ ማስታ□ቂያ በመለጠፍ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በመ/ቤቱ □ግዥ ዳይሬክቶሬት የሚካሄድ □ገበያ ጥናት መረጃን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመንና የቀረበለትን የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ ፋይል አድርጐ በመያዝ መጠቀም ይኖርበታል፡፡

፳፬.፱ የመንግስት መ/ቤቶች በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለሚ□ጽሙት ማናቸውም ግዥ እስከተቻለ ድረስ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

፳፬.፲ መ/ቤቱ ከዚህ በታች የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ በኤጀንሲው ሲፈቀድለት የዋጋ መጠየቂያ ለመላክና የዋጋ ማቅረቢያ ለመቀበል የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

ሀ/ የሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ መረጃ ሊደርሰው ከሚገባው አካል እና መረጃው ሊታወቅ ከሚገባው ቀን እና ሰዓት ውጪ በማንኛውም አካል ሊታይ እንደማይችል የሚያረጋግጥ የተሟላ የመረጃ ደህንነት ሲኖረው፣

ለ/ በአካባቢ ማስታወቂያ በመለጠፍ ሊወዳደሩ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሙሉ በዘዴው ለመጠቀም የሚያስችል ዕውቀት እና ዝግጁነት ያላቸው መሆኑ ሲያረጋግጥ፣

ሐ/ ከላይ በፊደል ተራ "ለ" የተቀመጠው ቢኖርም በኤሌክትሮኒክ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ ዋጋ መስጠት የማይችሉ በተለመደው አሠራር በፖስታ ዋጋ ሊሰጡ እንዲችሉ አማራጭ የተዘጋጀላቸው ሲሆን፣

፳፬.፲፩ መ/ቤቶች በዚህ የግዥ ዘዴ ግዥ ለመፈፀም የሚያወጡት ማስታወቂያ ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት አየር ላይ መቆየት ይኖርበታል፡፡ ማስታ□ቂጸ□· በፅል□ ፊ ረታ □ጸ የሚወጣውን ማስታወቂያ ይዘት ሊኖረው ይገባል፡፡

፳፬.፲፪ መ/ቤቶች ኤጀንሲው ለዚህ የግዥ ዘዴ ያዘጋጀውን መደበኛ □ፈ ረታ ሠነድ መሰረት አድርገው የሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ በተጫራቾች የሚቀርበው መወዳደሪያ ዋጋ ህጋዊ ሆኖ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ለመግዛት የሚፈለገው ዕቃ፣ አገልግሎትና የግንባታ ሥራ ዓይነትና ብዛት፣ የሚፈለገውን ዝቅተኛ የጥራት ደረጃና ከተጫራቹ የሚጠበቀውን ዝርዝር ዕጻ ታዎች ማመልከት ይኖርበታል፡፡

፳፬.፲፫ በዚህ አንቀጽ ለመጠቀም ሲባል የመንግሥት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይችሉም፡፡

## ፳፭. ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ፣

ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም የሚሰጠው ውሳኔ የሚከተሉትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

፳፫.፩ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ እና ፶፪ የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ሲሟሉ ይሆናል፡-

፳፫.፪ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ "መ" እና "ሠ" መሠረት በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን እና የምክር አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት እና አቅራቢው ፈቃደኛነት ላይ በመመሥረትና የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈጸም ይቻላል፡፡

ሀ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው ዕቃ፣አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ግዥ መጠን ቀደም ሲል ከተገዛው ከ፳፭% (ሀያ አምስት በመቶ) መብለጥ የለበትም፣

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሰረት ተጨማሪ ግዥ ለማዘዝ የቀድሞው ግዥ ውል ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ወይም ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ በሚቀጥሉት ፮ ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ የግዥ ትዕዛዙ መተላለፍ ይኖርበታል፣

ሐ/ በዚህ መሰረት ለሚፈፀም ግዥ በመጀመሪያው ውል ከነበረው የነጠላ ዋጋ የበለጠ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ አይፈቀድም፣

መ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሐ) የተቀመጠው ቢኖርም የመጀመሪያው ውል የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ እና የዋጋ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል የተባሉት ግብአቶች በተጨማሪው ውል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ በመጀመሪያው ውል ላይ በተመለከተው የዋጋ ማስተካከያ አሰራርና ስሌት መሰረት የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ግዥው ሊፈጸም ይችላል፡፡

፳፫.፫ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ "መ" እና "ሠ" መሠረት ቀደም ሲል የግንባታ ሥራዎችን ለማሰራት መ/ቤቱ ባወጣው ግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ አሸናፊ ከሆነው ሥራ ተቋራጭ ጋር በገባው የውል ሰነድ ውስጥ በተካተቱ ዲዛይኖች፣ ሥራ ዝርዝር፣ ስፔስፊኬሽን፣የግንባታ ዘዴዎች እና ዕቃዎች መቀየር፣ በውለታ ሰነዶች አለመጣጣም ፣በመሬት አቀማመጥና የአፈር ሁኔታ፣በአየር ሁኔታ መዛባት፣ ዋጋ ማቅረቢያዎች በቅድመ ዲዛይን ወቅት ሳይታዩ በመቅረታቸው ወይም በሚፈጠር የዲዛይን ችግር፣ ወይም ፍላጐት መቀየር ምክንያት በግንባታ ሥራው ላይ የሚከሰቱ የለውጥ ሥራዎችን የግንባታ ሥራውን እየሰራ በሚገኘው ሥራ ተቋራጭ የሚከተሉትን

አሠራሮች በመከተል ማሰራት ይቻላል፡፡

ሀ/ ለውጡ የግንባታ ሥራዎች መጨመርን፣ መቀነስን፤ መቀየርን፣ መተካትን፣ የጥራት ብዛት፣ ቅርጽ፣ ባሕሪ፣ ዓይነት፣ ቦታ፣ ልኬት፣ ከፍታ ወይም የመስመር ለውጦችን እና በተጠቀሰ ቅደም ተከተል፣ ዘዴ ወይም የመፈጸሚያ ጊዜ ለውጦችን ሊያካትት ይችላል፡፡

ለ/ ውል ፈጻሚዎች ወይም የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ የለውጥ ሥራ ሀሳብን ማመንጨት ይችላሉ፡፡ ሆኖም የሚቀርበው የለውጥ ሀሳብ የተግባራቱ መግለጫ፣ ወይም መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች እና የሚከናወኑበት ፕሮግራም፣ በንድፍ፣ የማሻሻያውን ባሕሪና ቅርጽ፣ዝርዝር መግለጫ፣ በሥራ ዝርዝር ዋጋ ማቅረቢያ መረጃ መደገፍ አለበት፡፡

ሐ/ በለውጥ ሥራ ዝርዝር ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ሥራዎች ባለቤት መ/ቤቱ ከተቋራጩ ጋር ውል ካልፈጸመና የለውጥ ትዕዛዞች እንዲከናወኑ ከአማካሪው መሀንዲስ ወይም ከክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ በጽሁፍ ካልተሰጠ መሥራት አይቻልም፡፡

መ/ ለሁሉም የለውጥ ሥራዎች ዋጋ በሚከተለው መሰረት ይወሰናል፡፡

(1) የግንባታ ሥራው በግንባታ ሥራ መጠን ዝርዝር ተመሳሳይ ባህሪና በተመሳሳይ ሁኔታዎች የሚፈጸም ከሆነ ውሉ ውስጥ ባለው የነጠላ ዋጋ መሠረት ይሰላል፡፡

(2) የግንባታ ሥራው ተመሳሳይ ባህሪይ የሌለውና በተመሳሳይ ሁኔታዎች ያልተከናወነ ከሆነ ሥራ ተቋራጩ አዲስ ነጠላ ዋጋ ከዝርዝር ትንተና ጋር እንዲቀርብ ተደርጎ የቀረበው የገበያ ዋጋ በሚደረግ ድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሠ/ ሆኖም የለውጥ ስራ የተከሰተበት ማንኛውም የስራ አይነት ላይ የተተከለው ዋጋ ያልተመጣጠነ ከሆነ ወይም ምክንያታዊ ሆኖ ካልተገኘ ወይም በቀድሞው ውል ውስጥ ለተመሳሳይ ስራ የተለያየ ዋጋ ካለ  የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ ተገቢ ነው የሚለውን ተመን ወይም ዋጋ ይወስናል ፡፡

ረ/ ማሻሻያው አስፈላጊ የሆነው የሥራ ተቋራጩ ውል በማፍረሱ ምክንያት ከሆነ ከዚህ ማሻሻያ ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ወጪዎች በሥራ ተቋራጩ ይሸፈናሉ፡፡

ሰ/ በለውጥ ትዕዛዝ ምክንያት የሚሰሩት አጠቃላይ የግንባታ ሥራዎች ዋጋ ከመጀመሪያው አጠቃላይ የውል ዋጋ ፳፭% /ሀያ አምስት በመቶ/ መብለጥ አይኖርበትም፡፡

ሸ/ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የለውጥ ስራዎች እንዳይከሰቱ የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ እና ውል ፈጻሚዎቹ በቅድመ ዲዛይንና በውለታ ሰነድ ዝግጅት ወቅት፣ በጨረታና በግንባታ አፈፃፀም ሂደት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል ፡፡

፷፫.፬ የመንግስት መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ "ሐ" በተገለጸው መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን አረጋግጠው ያልታሰቡና በመጀመሪያው ውል ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎችን ማሠራት ይችላሉ፡፡

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የመ/ቤቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

ለ/ በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ስራ የገንዘብ መጠን ከመጀመያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ፴% /ሠላሳ በመቶ/ የበለጠ መሆን የለበትም፣

ሐ/ በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ባለው ነጠ ላ ዋጋ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የነጠላ ዋጋው በመጀመሪያው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን መ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፷፫.፫ የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ተሽከርካሪና ማሽነሪ የሚያስፈልገውን መለዋወጫ ግልጽ ጨረታ በማውጣት ግዥ ለመፈፀም በጨረታ አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች የሚያቀርበው መለዋወጫ ተሽከርካሪ እና ማሽነሪዎቹ ረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል የአምራች ድርጅቱ ኦሪጅናል ምርት መሆኑን ማረጋገጥ የሚችል የቴክኒክ ባለሙያ የሌለው በመሆኑ ምክንያት ችግሩን ለመቅረፍ የተሻለው አማራጭ መለዋወጫዎቹን ተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎቹን በሀገር ውስጥ ለማቅረብ የአምራች ድርጅቱ ብቸኛ ውክልና ካለው ድርጅት በቀጥታ መግዛት መሆኑን ሲያረጋግጥ፣ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም በቅድሚያ መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የመንግስት መ/ቤቱ በቂ የገበያ ጥናት ማድረግ እና ሌላ የተሻለ አማራጭ ገበያ ላይ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ለሚጠቀምበት ተሽከርካሪና ማሽነሪ የሚገዛው መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡

፳፫.፮ የቅርብ ጊዜ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ፣ ዘመናዊና ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ተደርጎባቸው የተገዙ ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው ምክንያት ለተሽከርካሪዎቹ የሚመጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የጥገና ማሽነሪና ቁሳቁስ የተደራጀ ጋራጅ ያለው ተሽከርካሪዎቹን በሀገር ውስጥ ለማቅረብ የአምራች ድርጅቱ ውክልና ያለው ድርጅት ጋ ብቻ መሆኑንና ከዚህ ውጪ በሆነው አማራጭ ተሽከርካሪዎቹን በጨረታ አሸናፊ በሚሆነው ጋራጅ በማስጠገን ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በድርጅቱ በቀጥታ በማስጠገን የሚገኘው ጥቅም የተሻለ መሆኑን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሲያረጋግጥ፣

፳፫.፯ ግዥው ከሌላ አቅራቢ እንዲፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ፣

፳፫.፰ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ "ሰ" መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ ለጥናትና ለምርምር አገልገሎት የሚፈለግ፣ እና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ፣ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለመሥሪያ ቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ የሚከተሉትን አሠራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም ይቻላል።

ሀ/ ግዥውን በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለዚህ ሥራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል።

ለ/ የመንግስት መ/ቤቱ ግዥውን በለቀማ ሊገዙ የሚችሉ ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ጊዜያዊ ኮሚቴ በደብዳቤ ይሰይማል። እስከተቻለ ድረስ ስለሚገዛው እቃ ዕውቀት ያለው ሰራተኛ የኮሚቴው አባል እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

ሐ/ የተቋቋመው ጊዜያዊ ኮሚቴ ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለበት ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦት የሚኖርበትን ገበያ እና የገበያ ዕለት በመምረጥ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል።

መ/ ጊዚያዊው ኮሚቴው በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድሮ ግዥውን ይፈፅማል።

ሠ/ በግዥው አፈፃፀም ሒደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና አይነት፣ ግብይቱ የተፈፀመበት ቦታ፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስም እና አድራሻ የሚገልፅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል።

ረ/ በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓጓዙበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት የሚመለከተው ክፍል እንዲረከባቸው መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሰ/ ጊዜያዊው ኮሚቴ አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ-ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርሞ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡

፳፫.፱ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት:-

የመንግሥት መ/ቤቶች በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር ፫ሺ(አምስት ሺህ)ያልበለጡ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ወይም በጉዞ ወቅት ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር □ተያያ□ የቀጥታ ግዥዎችን የአካባቢውን □ፃጸ ዥፉ ባገናዘበ ሁኔታ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር ፳ ሺህ (ስልሳ ሺህ ብር) መብለጥ የለበትም፡፡

፳፫.፲ በአዋጁ አንቀፅ ፶፩.፩ (ሰ) በለቀማ እና ፶፩.፪ መሰረት ለሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ ሊገዛ ያሰበውን የግዥ አይነትና መጠን በመግለፅ አቅራቢው ሐሳቡን እንዲሰጥ በደብዳቤ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የሚላከው ደብዳቤ እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ እና አቅራቢው ዋጋን ጨምሮ የተሟላ ሐሳቡን እንዲያቀርብ የሚያስችለውን ማስረጃ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፳፫.፲፩ የመንግስት መ/ቤቱ ከአቅራቢው በፅሁፍ የቀረበለትን ዋጋን የጨመረ ሐሳብ ተቀብሎ በመመርመርና የዚህን መመሪያ እና የአዋጁን አንቀፆች እንደማይጥስ በማረጋገጥ ዋጋን ጨምሮ ድርድር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከለየ በኋላ ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡

፳፫.፲፪ በንዑስ አንቀፅ ፳፫.፱ ላይ በተመለከተው መሰረት ድርድር ለማድረግ የመንግስት መ/ቤቱ ተደራዳሪዎችን መምረጥ እና በአዋጁ አንቀጽ ፶፪.፪ መሠረት የሚደረገው ድርድር በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚሠጠውን አቅጣጫና የድርድር አትኩሮተ ነጥቦች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፳፫.፲፫ በአዋጁ አንቀፅ ፶፩.፩(ሰ) እና ፶፩.፪ መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈፅመው ግዥ የውል ስምምነት መፈረም ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ፺

## ልዩ ግዥ

## ፷፺. በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃና አገልግሎቶች ልዩ ግዥ

፷፺.፩ በሁሉም ወይም በተወሰኑ መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለግ ዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈፀመው የማዕቀፍ ስምምነትን መሠረት በማድረግ ሲሆን የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል::

ሀ/ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ላይ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል በቂ እና ግልፅ የሆነ የውስጥ አደረጃጀት በመፍጠር የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የመገምገም፣ የማፅደቅ እና ውል የማስተዳደር ስራዎች በተለያዩ ቡድኖች እንዲፈፀሙ ያደርጋል፣

ለ/ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጨረታ ዝግጅት እና ግምገማ ወቅት የሙያ ድጋፍ ከመንግስት መ/ቤቶች ሊጠይቅ እና ሊያገኝ ይችላል::

፷፺.፪ የልዩ ግዥ አፈጻጸም አዋጁን እና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለግዥው በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል::

፷፺.፫ በሁሉም ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የመንግሥት መ/ቤቶች የሚፈለጉ ተመሳሳይ ግዥዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው በሚከተሉት እና ይህንን መመሪያ ተከትሎ አሰራሩን ለማስፈፀም በሚወጡት ሰነዶች መሰረት ይፈፀማል::

ሀ/ ኤጀንሲው በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በመለየት ዝርዝር ያወጣል፤ ዝርዝሩንም በየጊዜው ያዳብራል፤ ለመንግስት መ/ቤቶች እና ልዩ ግዥ ለሚፈጽመው አካል ያሳውቃል፣

ለ/ እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት በተላለፈለት ዝርዝር መሰረት አመታዊ የግዥ ፍላጎቱን ልዩ ግዥ ለሚፈፅመው አካል እንዲያሳውቅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ (ማሳወቅ) አለበት፣

ሐ/ ልዩ ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል የሁሉንም የመንግስት መ/ቤቶች ፍላጎት በማሰባሰብ የግዥ እቅድ ያዘጋጃል፤ ያዘጋጀውን እቅድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፫ (ሐ) መሠረት ለኤጀንሲው እና ግዥው ለሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ያሳውቃል::

፳፮.፬ ልዩ ግዥ እንዲፈፅም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ለየግዥው የሚፈረመውን የውል አይነት እና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ይወስናል።

፳፮.፬.፩ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፮.፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ግዥ የሚፈጽመው አካል የሚከተሉትን ተጨማሪ ዝርዝሮች ያካተተ የግዥ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡-

ሀ/ የማስታወቂያ ጥሪ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ለመፈራረም እንዲቻል መሆኑን፣

ለ/ በማእቀፍ ስምምነቱ የሚፈፀመው ግዥ ዓይነት፣ ግምታዊ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቆይበትን ጊዜ

መ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙትን የመንግስት መ/ቤቶች ብዛት፣

፳፮፬.፪ ልዩ ግዥ በሚፈጽመው አካል ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለግዥው ማስፈጸሚያ የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉትን እንዲያካትት መደረግ አለበት፡-

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ዝርዝር እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የግዥ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ለ/ የማስረከቢያ ቦታ እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣

መ/ ግዥው የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈፃፀሙን፣

ሠ/ የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

፳፮.፭ በአዋጁ አንቀፅ ፳፩.፬ ላይ በተገለፀው መሰረት ለማዕቀፍ ስምምነት በወጣ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ጋር እስከ ሦስት አመታት ሊደርስ የሚችል ውል የሚፈረም ሲሆን የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል የሚከተሉትን እና ሌሎች ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንደግዥው ሁኔታ እና እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ፈቃደኛ ከሆኑ ተወዳዳሪዎች ጋር በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተመሳሳይ የሆነ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈርም ይችላል፡-

ሀ/ የሚፈለገው የግዥ መጠን እና የተመረጠው አቅራቢ አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን ሲሆን፣ ወይም

ለ/ በገበያው ላይ ያሉ ተመሳሳይ አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑና የግዥ ዕድሉን ለብዙ አቅራቢዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ወይም

ሐ/ የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ግዥውን በቀረበው ዋጋ በቶሎ ማጠናቀቅ ሲያስፈልግ፣

፳፯.፮ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፳፯.፭ ላይ በተገለጸው መሰረት በአሸናፊው ዋጋ እንዲያቀርቡ በደረጃቸው ቅደም ተከተል ሌሎች ተጫራቾችን ለውል ስምምነት ሲጋብዝ  የሚጋብዛቸውን አሸናፊዎች ቁጥር እንደ ግዥው ሁኔታ አይቶ ይወስናል::

በዚህ መሰረት የሚፈፀም ውል::

ሀ/ በአሸናፊው ዋጋ ለማቅረብ ፈቃደኛ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር ይፈረማል፣

ለ/ አሸናፊው ድርጅት ለውል ስምምነት እና ምርጫ ባላቸው ጉዳዮች የምርጫ  ቅድሚያ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

ሐ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፳፯.፭ ላይ የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ከጨረታው ዋና አሸናፊ ጋር የሚፈረመው የግዥ መጠን ከጠቅላላው ግዥ ከ፳ ፐርሰንት ያነሰ መሆን የለበትም::

፳፯.፯ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የመንግስት መሥሪያቤቶችን ወክሎ አጠቃላይ የውል ስምምነት የሚፈርም ሲሆን ስምምነቱም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚባሉ ሁኔታዎችን በግልፅ እንዲያካትት መደረግ አለበት:-

ሀ/ በውል ስምምነት አስተዳደር ወቅት በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶችን ዝርዝር፤ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚፈርመው እና የሚያስተዳድረውን አካል እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢዎች የሚኖራቸውን ኃላፊነት እና ግዴታ፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የግዥ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብ የሚደረግበትን፣ ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትል እና ግምገማ የሚደረግበትን ስርአት፣

ሐ/ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበትን ስርአት፣

፷፯.፰ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፷፯.፯ እና በአዋጁ ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል በማእቀፍ ስምምነት አስተዳደር ወቅት የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በውሉ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ይከታተላል፤

ለ/ ለማዕቀፍ ስምምነቱ ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፤ በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥም እንደአስፈላጊነቱ በመውረስ ገንዘቡን ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ያደርጋል፡፡ አቅራቢው የፈፀመውን ጥፋት በሚመለከትም በአዋጁ አንቀጽ ፸፰ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፯.፩ መሠረት ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፣

ሐ/ በማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው እና በመንግስት መ/ቤቱ መካከል አለመግባባት ሲፈጠ ር ጉዳዩን በውይይት ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤

መ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ ሁኔታ ላይ በጋራ ስምምነት ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልግ ይህንኑ ይፈፅማል፤

ሠ/ በውል አፈፃፀም ወቅት ለመንግስት መ/ቤቶች ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ ሲጠናቀቅ የውል አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ የውል ማስከበሪያው እንዲለቀቅ ያደርጋል፡፡

፷፯.፱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማእቀፍ ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

ሀ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሰረት ግዴታውን አለመወጣቱ ሲታወቅ፣

ለ/ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎት በግልጽ በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣

ሐ/ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የመንግስት መ/ቤቶችን ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

መ/ ከላይ በፊደል ተራ "ለ እና ሐ" መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቋረጥበትን ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን በመግለፅ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፣

ሠ/ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያው ጊዜ እስከሚጠናቀቅ በውሉ ላይ የተገለፁት መስሪያ ቤቶች ግዥያቸውን ከሌላ አቅራቢ መፈፀም አይችሉም፡፡

፳፮.፲ የመንግስት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት ከተሰጠው አካል የተላለፈላቸውን የማዕቀፍ ስምምነት ቅጂ በመጠቀም በውሉ ላይ የተገለፁትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ያስተላልፋሉ፡፡ መ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል ጋር በመመካከር ከአቅራቢው ጋር ተጨማሪ የተናጠል ውል መፈረም ይችላል፡፡

፳፮.፲.፩ የግዥ ትእዛዙ ወይም ተጨማሪው የተናጠል ውል በአጠቃላይ ውሉ ውስጥ የተካተቱ መሰረታዊ የሆኑ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎችን አይለውጥም፣ ሆኖም የመንግስት መ/ቤቱ በሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ጋር ሊስማማ ይችላል፡-

ሀ/ ዕቃው የሚቀርብበትን እና ክፍያ የሚፈፀምበትን ጊዜ ለማሳጠር፣

ለ/ በአንድ የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርበውን ዕቃ ብዛት ለመወሰን፣

ሐ/ ዕቃው የሚቀርብበትን ቦታ ለማሳወቅ ወይንም ለመቀየር፣

፳፮.፲.፪ መ/ቤቱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፳፮.፲.፩ በተገለፀው መሰረት የፈፀመውን የተናጠል ውል ቅጅ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽምና እንዲያስተዳድር ኃላፊነት ለተሰጠው አካል መስጠት አለበት፡፡

፳፮.፲፩ በማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይኖርባቸዋል፡

ሀ/ የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡት በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለሚፈፅመው አካል የገለፁትን ፍላጐት መሠረት በማድረግ በማዕቀፍ ስምምነት ግዥው የተፈፀመውን ዕቃ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ የተገለፁ በመንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙ ግዴታዎች በስምምነቱ መሰረት የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ በውሉ ላይ የሚነሱ አጨቃጫቂ ጉዳዮችን የማዕቀፍ ስምምነት ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በጋራ በመሆን ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣

መ/ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በዋና ዋና የውል ጉዳዮች ማለትም የዕቃ ጥራት እና መጠን ማጓደል፣ የማቅረቢያ ጊዜ አለመጠበቅ፣ በአስተሻሸግ እና በመሳሰሉ የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማዕቀፍ ስምምነቱን እንዲያስተዳድር ኃላፊነት ለተሰጠው አካል በወቅቱ በጽሑፍ ማሳወቅ፣

ሠ/ በማዕቀፍ ስምምነት ለተካተቱ ፍላጎቶቻቸው የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርብበትን መጠንና ጊዜ መለየትና ልዩ ግዥ የሚፈጽመውን አካል ስለአፈፃፀሙ ማማከር፣

፳፮.፲፪ የማዕቀፍ ስምምነት እንዲያስተዳድር ኃላፊነት ለተሰጠው አካል የመንግስት መ/ቤቶች ሥራ እንዳይጓተት የማዕቀፍ ስምምነት በወቅቱ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈረም አለመቻሉን ካረጋገጠላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚኖራቸውን ፍላጎት በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠበቅ መግዛት ይችላሉ፣

፳፮.፲፫ በአዋጁ አንቀፅ ፰፩ ንዑስ አንቀፅ ፫ መሰረት የመንግስት መ/ቤት በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ግዥውን በማዕቀፍ ስምምነት መፈፀም ይችላል፡፡

ሀ/ በመንግሥት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን/አገልግሎቶችን አሰባስቦ የማዕቀፍ ግዥ እንዲፈጽምና እንዲያስተዳድር ኃላፊነት ለተሰጠው አካል ሊፈፀም የማይችል ግዥ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተደጋጋሚ እና ለተከታታይ ጊዜ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣

ሐ/ የሚገዛው ዕቃ በሚሆንበት ጊዜ ዕቃውን አንድ ጊዜ ገዝቶ በመረከብ ለተከታታይ ጊዜ መጠቀም የማይቻል ወይም በየጊዜው ተጫራቾችን በማወዳደር ግዥውን መፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የማይኖረው ሲሆን፣

መ/ መ/ቤቱ ለግዥው ጸስያዘውን በጀት በተለያየ ጊዜ መጠቀም ሲኖርበት፣

፳፮.፲፬ በንዑስ አንቀፅ ፳፮.፲፫ መሰረት መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ለሚኖረው ተመሳሳይ ፍላጎት፡-

ሀ/ የሚያካሒደው ጨረታ በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፮ ላይ የተቀመጠውን ስርዓት መከተል አለበት፣

ለ/ የሚፈረመው ውል ከሁለት አመታት በላይ የቆይታ ጊዜ ሊኖረው አይገባም፣

ሐ/ መ/ቤቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮.፲፬ የተቀመጡ የዋጋ ማስተካከያ ድንጋጌዎችን የተከተለ የዋጋ ማስተካከያ ሊፈቅድ እና በተፈቀደው የአፈፃፀም ስርዓት መሰረት ሊፈጽም ይችላል፡፡

# ክፍል ፯

## የውል አስተዳደር

### ፳፯. ውልን ተፈፃሚ ማድረግ

፳፯.፩ የመንግስት መ/ቤቶች የተለየ ሁኔታ ካላጋጠማቸው በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፳፯.፪ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፳፯.፩ ላይ የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ የሚያስ ቀምጠው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል፡-

ሀ/ ውሉ ቅድሚያ ክፍያ እንዲፈፀም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና አቅራቢው እንዲያሲዝ በማድረግ የቅድሚያ ክፍያውን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዥዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ ሌተር አፍ ክሬዲቱን በፍጥነት መክፈት፣

ሐ/ በግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ ከላይ በፊደል "ሀ እና ለ" ከተቀመጡት በተጨማሪ በመሥሪያ ቤቱ ሊፈፀሙ የሚገባ ተግባራትን በውሉ መሰረት በወቅቱ ማከናወን፡፡

፳፯.፫ የመንግስት መ/ቤቶች ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

፳፯.፬ የመንግስት መ/ቤቶች የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግበው መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱም አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

፳፯.፭ የመንግስት መ/ቤት የግንባታ ዘርፍ ስራ ግዥ ሲፈፅም ክፍያ የሚፈፀመው የግንባታውን የክንውን ደረጃ መሠረት አድርጎ እና የሚከተለውን አፈፃፀም ተከትሎ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል፡፡

ለ/ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ ፲፮.፳፮.፱ ከተመለከተው በተጨማሪ ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ስራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግንባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን ፭% (አምስት በመቶ) በመያዣ መልክ ተቀንሶ ይያዛል፡፡

ሐ/ የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል (ለ) መሠረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ ፶% (ሃምሳ በመቶ) ለሥራ ተቋራጩ ይለቀቃል፡፡ ቀሪው ፶% (ሃምሳ በመቶ) ለአንድ አመት የጥገና ጊዜ ተይዞ ይቆያል፡፡ ሆኖም የሥራ ተቋራጩ ለ፲፪ ወራት የሚቆይ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና ካቀረበ የተያዘው ገንዘብ ሊለቀቅለት ይችላል፡፡

መ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ የክፍያ የምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ በ፲፬ የሥራ ቀናት ውስጥ መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት፡፡

ረ/ አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል (መ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በመ/ቤቱ ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የአማካሪ መሐንዲሱ ኃላፊነት ለአገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

ሰ/ መ/ቤቱ ያለበቂ ምክንያት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል (ሠ) ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአማካሪ መሐንዲሱ በቀረበለት ማረጋገጫ መሠረት ክፍያ ባይፈፅም ተቋራጩ በውሉ መሰረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

## ፳፰ የውል አፈፃፀምን መከታተል

፳፰.፭ የመንግስት መ/ቤቶች የውል አፈፃፀምን የሚከታተል አካል መለየት ወይም የውል ክትትል በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚፈፀም በሚሆንበት ወቅት አካላቱ ተግባራቸውን በግልፅ እንዲያውቁ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

፳፰.፮ የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው የመንግስት መ/ቤቱ አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል::

፳፰.፯ የመንግስት መ/ቤቱ በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል:-

ሀ/ ተከታታይ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም፣

ለ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ መስጠት፣

ሐ/ አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ሕጋዊ የሆነ እገዛ በማድረግ የውሉ አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል::

፳፰.፰ በውል አፈፃፀም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የመንግስት መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም::

፳፰.፱ በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት የመንግስት መ/ቤቶች በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይኖርባቸዋል:-

ሀ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውል ስምምነቱን ሁኔታዎች ጠብቆ በወቅቱ መክፈት፣

ለ/ ተቀባይነት የሚኖራቸውን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

ሐ/ ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፤ የሌተር ኦፍ ክሬዲት፤ የዋራንቲ መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

መ/ የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፤ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ ለማከናወናቸው ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን፣

ሠ/ ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ

፳፰.፯ የመንግስት መ/ቤት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፳፱. ውል ማጠናቀቅ

፳፱.፩ የመንግስት መ/ቤት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎችና እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውሉ መጠናቀቁን ማረጋገጥ አለባቸው ለዚህም:-

ሀ/ አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፣ ዕቃ፣ የምክር ወይም ሌሎች አገልግሎቶች ማቅረቡን፣

ለ/ በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች፣ ዋራንቲዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣

ሐ/ በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን፣ ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሰረት አገልግሎት መገኘቱን፣

መ/ ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ከአጓጓዦች፣ ከጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ የመንግስት መ/ቤቱ ጥቅሞች መከበራቸውን እና የመንግስት መ/ቤቱ ግዴታዎች የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፣

፳፱.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ፰

# ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፴. መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር፣

፴.፩ የመንግስት መ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠብቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት ለኤጀንሲው ጥያቄያቸውን አቅርበው ሲፈቅድላቸው ብቻ ነው::

፴.፪ መ/ቤቶች ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፴.፩ በተገለጸው መሠረት የሚቀርቡት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያየዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብ ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ለኤጀንሲው ማቅረብ አለባቸው::

## ፴፩. የግዥ ሠነዶች

፴፩.፩ መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀፅ ፳፫ ላይ የተዘረዘሩት እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የግዥ ሰነዶች ማለትም፡-

ሀ. ለጨረታው ያዘጋጁትን የጨረታ ማስታወቂያ፣

ለ. ለጨረታው ያዘጋጁትን የጨረታ ሠነድ፣

ሐ. በጨረታው የተሳተፉት ተጫራቾች ሞልተው ያስገቡት የመጫረቻ ሠነድ፣

መ. በጨረታ መክፈቻ ሥነ ስርዓት ላይ የተያዘ ቃለ-ጉባኤ፣ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች/ወኪሎች ዝርዝር፣

ሠ. በሁለት ፖስታ የቀረበ ጨረታ ከሆነ የቴክኒክ ግምገማ፣ የፋይናንስ ግምገማ የተደረገበት ቃለ-ጉባኤ እንዲሁም የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የግምገማ የውሳኔ ሀሳቡን ለማጽደቅ ባደረገው ስብሰባ የተያዘ ቃለ-ጉባኤ፣

ረ. ተጫራቾች ለጨረታው ያቀረቡት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና፣

ሰ. የጨረታ ግምገማ ውጤት ለአሸናፊና ተሸናፊ ተጫራቾች የተገለፀበት ደብዳቤ ወይም ማስታወቂያ፣

ሸ. በጨረታው ሂደት ላይ ከዕጩ ተጫራቾች አቤቱታ ቀርቦ ከሆነ የቀረበውን አቤቱታ፣ መ/ቤቱ የሰጠውን ምላሽ የሚያሳ ሠነድ፣ በቦርዱ ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነም ውሳኔ የተሰጠበትን ሠነድ፣

ቀ. አሸናፊው ተጫራች ያቀረበው የውል ማስከበሪያ እና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና፣

በ. መ/ቤቱ አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር የተፈራረመው የውል ሠነድ፣

ተ. ርክክብ የተፈፀመበት ሠነድ፣

ቸ. ለተፈፀመው ግዥ ለክፍያ የቀረቡትን ደጋፊ ሰነዶች ጨምሮ ክፍያ የተፈፀመባቸውን አጠቃላይ የወጪ ማስመስከሪያዎች፣

ነ. በግዥ አፈፃፀም ሂደት ከዕጩ ተጫራቾች፣ ከተጫራቾች እና ከአቅራቢዎች ጋር በፁሁፍ የተደረጉ ግንኙነቶች ካሉ ሁለቱም ወገኖች የፃፉትን ደብዳቤዎች፣ የያዙትን ቃለ-ጉባኤዎች እንዲሁም፣

ኘ. ሌሎች ከተፈፀመው ግዥ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሠነዶች በተፈፀሙበት ቅደም ተከተል መሠረት በፋይል አደራጅተው ይዘው ማቆየት ይኖርባቸዋል::

፴፩.፪ የግዥ ሰነዶች በክልሉ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፳፰ /፪ሺ፪ አንቀፅ ፳፯ ላይ በተገለፀው መሰረት በሚወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ላይ ለፋይናንስ ሰነዶች የቆይታ ጊዜ ከሚገለፀው እኩል የቆይታ ጊዜ ይኖራቸዋል::

፴፩.፫ በክልሉ መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፫፵፮/፪ሺ፬ አንቀጽ ፰ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በአንድ ግዥ ፈፃሚ አካል እንዲፈጸም በየጊዜው ከሚወሰኑት ግዥዎች በስተቀር በክልሉ መንግስት መ/ቤቶች የሚፈፀሙት የግንባታ ሥራዎች፣ የዕቃዎችና የአገልግሎት ግዥዎች በሙሉ በጀቱን በሚያስተዳድረው ወይም የበጀቱ ባለቤት በሆነው መ/ቤት መ□ናም ይኖርበታል:: ግዥው የተፈፀመባቸው አጠቃላይ ሠነዶችም በዚሁ መ/ቤት ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል::

፴፩.፬ በንዑስ አንቀጽ ፴፩/፫ □ተቶለና□ እንደተጠበቀ ሆኖ በግንባታ ሥራዎች ግዥ አፈፃፀም ሂደት የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ እና ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል:-

፴፩.፬.፩ የክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ እና በተዋረድ ከዞን እስከ ከተማ አስተዳደር በኮንስትራክሽን ዘርፍ ያሉ አካላት ተግባርና ኃላፊነቶች

ሀ. የሚገነባውን የግንባታ ሥራ ዲዛይን፣ የግንባታውን ዝርዝር ሥራ፣ □መ□ቴ□ሪጸ መስፈርቶችና ሌሎች ቴክኒክ ነክ የሆኑ ሥራዎችን በ□ርኘ ባለ□ የአሰራር ሥርዓት መሰረት በማዘጋጀት ለፈፃሚ መ/ቤቶች ይልካል::

ለ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥ ገምጋሚ ቡድን አባል በመሆን ጨረታውን □ሚጸካሂድና ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከተገባም በኂላ ግንባታ□ በውሉ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን የውል ቁጥጥር በማድረግ የክፍያ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት እና ሌሎች አስፈላጊ ሪፖርቶችን እጸ□ፉ□ ለዕ ዴ ፈፃሚው መ/ቤት የሚያቀርብ ቢቻል በፊደል ተራ ሀ ላይ የተገለፁትን ሥራዎች ካከናወነው ባለሙያ ውጪ የሆነ የቴክኒክ ባለሙያ ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች ይልካል::

፴፩.፬.፪ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ተግባርና ኃላፊነቶች

ሀ. በኮንስትራክሽን ቢሮ ለግዥው የተዘጋጁትን ሠነዶች አጠቃላይ የጨረታ

ሠነዱ አካል በማትረፅ □ፊ ረታ ማስታ□ቂጸ ጸ□□ል፣ ከባለስልጣኑ
የሚላከውን ባለሙያ አባል በማድረግ ጊዚያዊ የግምገማ ቡድን ያቋቁማል፣
ፊ ረታ□ ⶸንዲገመገም ያደርጋል፣ አጠቃላይ የግዥ ሂደቱን ያከናውናል::
ለ. ስለክፍያ አፈፃፀም በውል ሠነዱ ላይ የተቀመጠውን መሠረት በማድረግ
ጁቆ□□ራል፣ አጠቃላይ የግዥ ሂደቱን አፈፃፀም የሚያሳዩ ሠነዶችን
በአግባቡ አደራጅቶ በመያዝ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ አቅርቦ
ጸስመረምራል::

# ፴፪. የአቅራቢዎች ምዝገባ እና በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

## ፴፪.፩ የአቅራቢዎች ምዝገባ፣

በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ ነው::

ሀ/ በመንግሥት ግዥ መሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች የዞንና ልዩ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች በሚያከናውኑት የአቅራቢዎች ምዝገባ መመዝገብ የሚኖርባቸው ሲሆን መ/ቤቶቹም የተመዝጋቢዎችን ዝርዝር ወዲያውኑ ለኤጀንሲው መላክ ይኖርባቸዋል ::

ለ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተገለጸው ቢኖርም በሪል ስቴት ያልተሠማሩ የቤት አከራዮች በአቅራቢዎች ዝርዝር ባይመዘገቡም ለቤት ኪራይ በወጣ ጨረታ መሳተፍ ይችላሉ፣

ሐ/ የንግድ ድርጅቶቻቸው ከክልሉ □ቸ □ሚቆኙ አቅራቢዎች በየትኛውም ድርጅቶቻቸው በሚገኝበት አካባቢ በተዘረጋው የአቅራቢዎች የምዝገባ ሥርዓት ስለመመዝገባቸው ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች በሚያወጡት ጨረታ□መሳተአ ይችላሉ::

## ፴፪.፪ በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች:-

ሀ/ አቅራቢው የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልፅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣

ለ/ የምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ ስለተሰማራበት የሙያ ዘርፍ በሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ሐ/ በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሥራ ተቋራጭነት ሥራ እንዲሠራ በፌዴራል ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም በክልሉ ኮንስትራክሽን ቢሮ የተሠጠውን ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ፣

መ/ የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ ከክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የተሠጠ ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ፣

ሠ/ መድሐኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከፌዴራል ወይም ከክልሉ ጤናና ጤና ነክ አገልግሎት ግብዓቶች ጥናትና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሠጠውን ማስረጃ፣

# ክፍል ፱

## የመንግሥት ግዥ ሥነ-ምግባር

### ፴፫. ከግዥ ባለሙያ የሚጠበቅ ሙያዊ ሥነ ምግባር

በአዋጁ አንቀጽ ፴፪.፩ ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ከመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ተግባሩን በተሟላ የሙያ ሥነ-ምግባር መፈጸም ይኖርበታል:: ለዚህም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን አለበት:-

፴፫.፩ በመንግስት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጽሑፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ሥራ ራሱን ማግለል ይኖርበታል::

፴፫.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ሲደርሰው:-

፴፫.፪.፭ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፴፫.፪.፮ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፴፫.፪.፭ በተሰጠው የጽሑፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል፣

፴፫፪.፫ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፴፫.፪.፮ ላይ በተቀመጠው መሠረት የመንግሥት መ/ቤቱ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ:-

ሀ/ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሂደቱ እንዲገለል ያደርጋል::

ለ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደገና እንዲታዩ ያደርጋል::

ሐ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሠራተኛው ወይም በኃላፊው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል::

፴፫.፫ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈፀም ዕድል እንዳያገኙ የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈፀም የለበትም:: ለዚህም::

ሀ/ በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልፅ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፣

ለ/ በጨረታ ሰነዱ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሐ/ የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ጊዜ መገለጹን ማረጋገጥ፣

መ/ በውል ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና እስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ሠ/ በውል አፈጻጸም ወቅት ክፍያን፣ ቁጥጥርን፣ የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉት ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

፴፫.፩ በመንግሥት ግዥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች እና ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ ከሦስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም። ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች የሚከተሉትን ያካተተ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል:-

ከዚህ በታች በተራ ፊደል (ሠ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

ሀ/ የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ በተለይ ለመንግሥት መ/ቤቱ ከአቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል አለመቀበል፣

ለ/ የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

ሐ/ በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለመንግሥት መ/ቤቱ አቅራቢ/ዕጩ አቅራቢ ከሆነ አካል የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

መ/ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል፣ ሆኖም ጉዞን ያላካተተ እና ጋባዡ ከመንግሥት መ/ቤቱ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ጋር የማይገናኝ ግብዣ ሲሆን ሊቀበል ይችላል።

ሠ/ ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተቀመጠው ቢኖርም ሠራተኛው ወይም ኃላፊው አቅራቢው/ዕጩ አቅራቢው ለማስታወቂያነት አገልግሎት የሚያዘጋጃቸው የውስጥ እሴት እንጂ የገበያ ዋጋ የሌላቸው በነጻ የሚታደሉ ስጦታዎችን መቀበል ይችላል።

፴፫.፪ የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስራ አጋጣሚ የተመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸምም:-

ሀ/ የሚያደርገው ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ/ እራሱን የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማንኛውም ተግባር መጠበቅ ይኖርበታል።

፴፫.፯ የመንግሥት መ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከግዥ ሥራ ጋር በተገናኘ ያወቃቸውን የመንግሥት መ/ቤቱን ወይም የዕጩ ተወዳዳሪውን ወይም የአቅራቢውን ሚስጥራዊ መረጃ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም:-

ሀ/ ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጥ ወይም የመንግሥት መ/ቤቱን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ በልዩ ሁኔታ በመ/ቤቱ ኃላፊዎች ካልተፈቀደ በስተቀር ለማንኛውም አካል አለመስጠት፣

ለ/ የመንግሥት መ/ቤቱ በውል አፈጻጸም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የመንግሥት መ/ቤቱን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፣

ሐ/ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት ውጤቱ በመንግሥት መ/ቤቱ ከመገለጹ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ፣

## ፴፬. ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ ምግባር

በመንግሥት ግዥ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በአዋጁ አንቀጽ ፴፪.፪ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥነ-ምዕባር መርሆዎች መከተል አለባቸው:-

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ራሱ ወይም በሦስተኛ ወገን በኩል በአንቀጽ ፴፫.፬ ሥር የተጠቀሰውን ስጦታ መስጠት የለበትም፡፡

ለ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የመንግሥት መ/ቤቱ በግዥ አፈጻጸም ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ለሚወስደው ውሳኔ የሚረዳ ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም አቅራቢው የሚያውቀውን መረጃ ለመንግሥት መ/ቤቱ መግለጽ አለበት፡፡

ሐ/ የመንግሥት መ/ቤት በሚያደርገው የግዥ አፈጻጸም በመስኩ ከተሰማራ ሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመነጋገር ዋጋ መስጠት ወይም ላለመስጠት፣ መ/ቤቱን ሊጎዳ የሚችል መረጃ መለዋወጥ ወይም በግዥ አፈጻጸሙ ለመሳተፍ የሌላ ተወዳዳሪን ሰነድ ወይም መረጃ መጠቀም የለበትም፡፡

መ/ በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም የተመለከተውን የሙስና ተግባር ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ የሙስና ተግባሩ ተባባሪ ሆኖ መገኘት የለበትም፡፡

# ክፍል ፲

## በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብ አቤቱታ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ቦርድ

## ፴፩. የቦርድ አባላት ስያሜና የስራ ዘመን

ሀ/ የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሀላፊ ከእጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ከተጫራቾች በመንግስት መስሪያ ቤቶች የግዥ አፈጻጸም ላይ የሚቀርብን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ የሚሰዓ :

ከክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወከል ................. ሰብሳቢ፣

ከክልሉ ንግድ ምክር ቤት የሚወከል.......................................... አንድ አባል፣

ከክልሉ መንግሥት መ/ቤቶች የሚመረጥ ..................................አንድ አባል፣

ከክልሉ መንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚወከል........................... አንድ አባል፣

ከክልሉ መንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚወከል...አንድ አባል፣

በድምሩ አምስት የቦርድ አባላትን የሚሰይም ሲሆን ፣ ከኤጀንሲው አንድ ባለሙያ ድምፅ የሌለው አባል ሆኖ በፀሐፊነትና በአስረጂነት እንዲሰራ ይመደባል።

ለ/ የቦርዱ አባላት በተቻለ መጠን በስምምነት ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል። የአባላት ድምጽ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

ሐ/ የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው። ሆኖም የስራ አፈጻጸማቸውና ያላቸው ስነ-ምግባር ታይቶ ለሌላ አንድ ተመሳሳይ የስራ ዘመን እንዲሰሩ ሊራዘም ይችላል።

መ/ ለቦርድ አባልነት የሚሰየሙት በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር በቂ እውቀትና ልምድ ያካበቱ፣መልካም ባህሪና ስነ-ምግባር ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

ሠ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሰብሳቢው በስብሰባው ላይ የማይገኝ ሲሆን፣ ስብሰባውን በጊዜያዊነት የሚመራለት ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል ሊወክል ይችላል።

## ፴፪. የቦርድ ስብሰባ

ሀ/ የቦርድ አባላት ስራቸውን ለማከናወን እንደአስፈላጊነቱ በሳምንት አንድ ቀን የሚሰበሰቡ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ የስብሰባ ቀን ሊወስኑ ይችላሉ፣

ለ/ ከቦርድ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል

## ፴፫. ከቦርድ አባልነት መልቀቅ

የቦርድ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በማንኛውም ጊዜ ከቦርድ አባልነት መልቀቂያ ማመልከቻ ለቢሮ ሀላፊው በማቅረብ ሲፈቀድላቸው መልቀቅ ይችላሉ፡፡

## ፴፰. የቦርድ አባልነት መቋረጥ

የቢሮ ሀላፊው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የቦርድ አባልን አባልነት ሊያቋርጥ ይችላል፡

ሀ/ በአዕምሯዊ ወይም በአካላዊ ጉዳት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ፣

ለ/ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ፣

ሐ/ የሥነ-ምግባር ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት ከተገኘበት፣

መ/ ያለ በቂ ምክንያት በ፫ /ሶስት/ ተከታታይ የቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ካልተገኘ

## ፴፱. የጥቅም ግጭትን ስለመግለጽ

ማንኛውም የቦርዱ አባል ከአቤቱታ አቅራቢ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት ግዥ አፈጻጸም ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ግንኙነት ካለው ይህንኑ ለቦርዱ በማሳወቅ ከቦርዱ ስብሰባ ራሱን ማግለል አለበት፡፡

## ፵. የቦርዐ ስልጣን

ቦርዱ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አሸናፊውን ተጫራች ከመምረጥ ወይም ውል ከመፈረም ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ከማሳለፍ በስተቀር የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ህግ ከሚያዘው ውጭ ስለመፈጸሙ ወይም ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ ወይም የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈጸሙ ወይም የጥቅም ግጭት ወይም የሙስና ተግባር ስለመፈጸሙ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ከግዥው ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች፣ መዝገቦችና መግለጫዎች ከመንግሥት መ/ቤቱ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

ለ/ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመንግሥት መ/ቤቱ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁአ ማስታወቂያ መላክ፣

ሐ/ የቀረበው አቤቱታ በኤጀንሲው ወይም በሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝር የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎበት ሪፖርት እንዲቀርብለት የማድረግ፣

መ/ ምስክሮችን የመጥራት፣ ምስክሮችና ግዥው የሚመለከታቸው ወገኖች ቃላቸውን በመሃላ እንዲሰጡ የማድረግ፣

ሠ/ የመንግሥት መ/ቤቱ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ስራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የማስተላለፍ፣

ረ/ የመንግሥት መ/ቤቱ ከህግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን የማድረግ፣

ሰ/ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው የተጫራቹን ወይም የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ የማድረግ፣

ሸ/ አቤቱታው ለቦርዱ የቀረበው የመንግሥት መ/ቤቱ ለአቤቱታው ምላሽ ከሰጠ በኋላ ፭ የሥራ ቀናት አልፎ ከሆነ ወይም አቤቱታ□ በመጀመሪያ ለመንግሥት መ/ቤቱ ያልቀረበ ከሆነ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ፣

## ፴፩. የቦርዱ ተግባር

ቦርዱ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ አቤቱታ ከዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ከተጫራች መቀበል፣

ለ/ አቤቱታው ለቦርዱ የቀረበው ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ ለመንግሥት መ/ቤቱ አቤቱታውን አቅርቦ መልስ በተሰጠው ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ወይም መስሪያ ቤቱ መልሱን አዘግይቶ ከሆነ አቤቱታው ለመ/ቤቱ ከቀረበ ከ፲ኛው ቀን በኋላ ባሉት ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ መሆኑን ማጣራት፣

ሐ/ አቤቱታው የቀረበው በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከሆነ አቤቱታ ለቀረበበት የመንግሥት መ/ቤት አቤቱታ የቀረበበት መሆኑንና ከግዥው አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ሰነዶችንና መግለጫዎች እንዲልክ እና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁፉ ማስታወቂያ መላክ፣

መ/ የጽሑፍ ማስታወቂያ የደረሰው የመንግሥት መ/ቤት የግዥ ሂደት የተከናወነባቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና መግለጫ እንዲልክ መከታተል፣

ሠ/ ከቦርዱ □/ቤት ተጠናቅረው የቀረቡትን የአቤቱታውን ጭብጦች፣ ከመንግሥት መ/ቤቱ የተሰጠውን ምላሽ፣ ማስረጃዎች፣ ሰነዶችና መግለጫዎች ከመንግሥት የግዥ ህግ አኳያ በመመርመር ውሳኔ መስጠት፣

ረ/ ውሳኔውን ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፉ እንዲደርስ ማድረግ፣

ሰ/ ስለተከናወኑ ተግባራት ለቢሮ□ ሀላፊ ሪፖርት ማቅረብ፣

# ክፍል ፲፩

## ለመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

### ፵፪. የዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች አቤቱታ የማቅረብ መብት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፫ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል  ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት ወይም ሂደቱ እንዲጣራለት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለቦርድ ጽ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

### ፵፫. አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች

ከዚህ በታች በተመለከቱ ምክንያቶች አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡

ሀ/ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጁ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወሰነው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ፣

ለ/ በውስን ጨረታ ለሚፈጸም ግዥ በተከናወነ የተጫራቾች አመራረጥ ወይም በጨረታ ሠነዱ ላይ አስቀድሞ በሰፈረ የተጫራቾች ማወዳደሪያ መስፈርት ላይ፣

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫  እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮.፳.፩ መሠረት ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች፣ ምርቶችና እና የግንባታ ዘርፍ ስራዎች በተሰጠ ልዩ አስተያየት ላይ፣

መ/ በአዋጁ አንቀጽ ፴ መሰረት ጨረታን፣ የመጫረቻ ሰነድን  ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሳኔ ላይ፣

ሠ/ መ/ቤቱ የግምገማውን ውጤት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔውን በጽሁፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ /አምስት/ የስራ ቀን ካለፈ፡፡

ረ/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፮  ንዑስ አንቀጽ ፫ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ "ሀ" በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ፯ የሥራ ቀናት ካለፈ በኋላ ውል የተፈረመ ከሆነ፣

## ፴፬. ለመንግሥት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የሚቀርብ አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት

### ፴፬.፩ የግዥ ውል ከመፈረሙ በፊት፣

ሀ/ ጨረታውን ያወጣው የመንግሥት መ/ቤት የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጠ ›ት ለተጫራቾች ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ተጫራቾች አቤቱታ ካላቸው ማቅረብ እንዲችሉ ፯ የስራ ቀናት ሊጠብቃቸው ይገባል፡፡

ለ/ በግዥ አፈጻጸም ሂደት ጉዳት ወይም በደል ደርሶብኛል የሚል አቅራቢ ወይም ተጫራች ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ በይፋ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው የመንግሥት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለመ/ቤቱ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ሐ/ አቤቱታ ባቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው የመንግስት መ/ቤት በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ ፸፫ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተጠቀሰው መሠረት የመንግስት መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበው አቤቱታ ውሳኔውን በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

መ/ የመንግሥት መ/ቤቱ ውሳኔውን በሰጠ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ቅጅ አቤቱታውን ላቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

### ፴፬.፪ በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበ ጨረታ፣

ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ የመጫረቻ ሰነዳቸውን በተለያየ ሁለት ኤንቬሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

ሀ/ □ቴክኒክ የግምገማ ውጤቱን የመንግሥት መ/ቤቱ ለሁሉም በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑ ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ ያሳውቃል፣

ለ/ ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም የግዥ አዋጁን፣ የአፈፃፀም መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ

ካለው፣ቅሬታውን በ፫ የሥራ ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ በማሳሰብ የመንግሥት መ/ቤቱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች ባሳወቀበት ደብዳቤ ይገልፃል፡፡

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ለቀረበው አቤቱታ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተሰጠው ውሳኔ የግዥ አዋጁን፣ መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን የጠበቀ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ተጫራች የኃላፊውን ውሳኔ ባወቀ በ፫ የሥራ ቀናት ውስጥ ቀጣይ አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

መ/ የመንግሥት መ/ቤቱ የዋጋ መወዳደሪያ ሀሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾቹ ካሳወቀ ፫ ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ቀጣይ አቤቱታ የቀረበ ከሆነ መ/ቤቱ የዋጋ መወዳዳሪያ ሀሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሳይከፍት ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል፡፡

፵፬.፫ አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ የክልሉን መንግስት የግዥ አዋጅና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል፡፡

## ፵፭. የመንግሥት መ/ቤቱ የግዥ አፈጻጸም ሂደትን ማገድ ስለመቻሉ

ሀ/ ጨረታውን ያወጣው የመንግስት መ/ቤት አቤቱታው ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፵፬.፪ ፊደል ተራ ለ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን ካረጋገጠ አቤቱታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ለ/ በመንግስት መ/ቤት የሚተላለፍ ማናቸውም ውሳኔ እንዲሁም የውሳኔው ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዥውን ስርዓት የሚያሳዩ ሰነዶች አካል ሆነው መያዝ አለባቸው፡፡

## ፵፮. አቤቱታ ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብበትና የሚጣራበት ስርዓት

ሀ/ በአዋጁ አንቀጽ ፸፫ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ አቤቱታ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ፲ □ሥራ ቀናት ውሰጥ ለአቤቱታው ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ውሳኔ ተሰጥቶ አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ የመስሪያ ቤቱ ውሳኔ በጽሁአ ከተገለጸለት ወይም ውሳኔ ካልሰጠ ውሳኔውን መስጠት ከነበረበት ቀነ ገደብ ማብቂያ ጀምሮ በሚቆጠር ፫ የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን

ለቦርድ ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለቦርድ ጽ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ለ/ እጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ አቤቱታውን ለቦርድ ጽ/ቤት ሲያቀርብ ለመሥሪያ ቤቱ ያቀረበውን አቤቱታ የሚያሳይ ደብዳቤ፣ በመንግስት መስሪያ ቤት ለአቤቱታው ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ የውሳኔውን ቅጂ፣ የአቤቱታውን ጭብጥና፣ ተያያዥ ማስረጃዎችን በአባሪነት ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የቦርዱ ጽ/ቤት አቤቱታው እንደቀረበለት ወዲያወኑ አቤቱታ የቀረበ መሆኑን፣ በቀረበበት አቤቱታ□ ላይ ያለውን ማስረጃና መግለጫ ማስታወቂያው በደረሰው በ፭ የሥራ ቀናት ውሰጥ እንዲያቀርብ እንዲሁም ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረሰ ቀጣይ የግዥ ሂደት እንቅስቃሴ እንዲያቆም የሚገልጽ ማስታወቂያ ለመንግስት መ/ቤቱ ይልካል፡፡

መ/ አቤቱታ የቀረበበት የመንግስት መ/ቤት ከቦርድ ጽ/ቤት እንዲያቀርብ የተጠየቀውን ግዥ የፈፀመባቸው ሠነዶችና መግለጫ ማስታወቂያ ከተላከለት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሠ/ ቦርዱ አቤቱታ□ የቀረበበትን ማናቸውንም ግዥ የሚያጣራው እና ውሳኔ የሚሰጠው መ/ቤቱ ለጨረታው ያዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ የግዥ አዋጅ፣ መመሪያ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ግምገማ ሪፖርቱን፣ ተጫራቹ ያቀረበውን የመጫረቻ እና ሌሎች ሠነዶችን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

ረ/ ቦርዱ ከላይ ፊደል ተራ "መ" የቀረቡለትን ሰነዶች መርምሮ ውሳኔውን በ፲፭ የሥራ ቀናት ውሰጥ በጽሁፍ አቤቱታ ላቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች እና ለመ/ቤቱ መስጠት አለበት፡፡

ሰ/ የቦርዱ ጽ/ቤት ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ ወዲያውኑ አቤቱታውን ላቀረበው አቅራቢ ወይም ተጫራች እና አቤቱታ ለቀረበበት የመንግሥት መ/ቤት እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ፲፪

## ለኤጀንሲው የሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚታይበት ሥርዓት

### ፹፯. የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበትና የሚጣራበት ሥርዓት

ኤጀንሲው በአዋጁ አንቀጽ ፷፭ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ላይ የሚያቀርቡትን የጥፋተኝነት ሪፖርት በሚከተለው ሁኔታ አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፵፯.፩ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት በመንግሥት ግዥ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች/አቅራቢ በተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ሕግ ከሚያዘው ውጭ መፈፀሙን፣□ልለመ□ናም□ቃ□ኛ አለመሆኑን ማጭበርበሩን፣ የሀሰት ሰነድ ማቅረቡን፣ መመሳጠሩን፣ የሙስና ተግባር መፈፀሙን እና/□ጁም የገባውን  የውል ግዴታ ባለመፈፀሙ  ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማረጋገጥ ከቻለ በጥፋት ፈፃሚው ተጫራች/አቅራቢ ላይ የጥፋተኛነት ሪፖርት ለኤጀንሲው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፵፯.፪ የመንግሥት መ/ቤቱ በተጫራቹ ወይም አቅራቢው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲያቀርብ የአቤቱታውን ጭብጥ የሚገልጽ መግለጫ፣ ግዥ የተካሄደባቸውን ሰነዶች ቅጂና ሌሎች ጉዳዩን ለማጣራት የሚረዱ ተያያዥ ማስረጃዎችን አንድ ላይ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፵፯.፫ ኤጀንሲው ሪፖርት ለቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት ፍሬ ሀሳብ በመግለጽ ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በበኩሉ ያለውን ማስረጃ እና ማብራሪያ በ፭ □ሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው እንዲያቀርብ የጽሑአ ማስታወቂያ መላክና አፈፃፀሙን መከታተል ይኖርበታል፡፡

፵፯.፬ ኤጀንሲው ከመንግሥት መ/ቤቱ እንዲሁም ከተጫራቹ ወይም ከአቅራቢው የቀረቡለትን መግለጫና ማስረጃዎች ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ፣ ከጨረታ ሰነዱና ከግዥ ውሉ አኳያ በማጣራት የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውሰጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ሪፖርት ላቀረበው የመንግሥት መ/ቤት እና የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት አቅራቢ ወይም ተጫራች እንዳስፈላጊነቱም ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ይልካል፡፡

፵፯.፭ በኤጀንሲው የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ □አዋጁን አንቀጽ ፷፭ (፭) የተከተለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ  ፵፯ ፭.፩፣ ፵፯ ፭.፪ □ጁም ፵፯ ፭.፫ ላጁ ከተመለከቱት መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል  ፡፡

፵፯.፭.፩ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የግዥውን ግምገማ ውጤት ሆን ብሎ ለማዛባት ወይም ለማስለወጥ በጨረታው ሂደት ወይም በውል አስተዳደር ወቅት

ከዚህ በታች የተገለጹትን መፈፀሙ ከተረጋገጠ እንደነገሩ ሁኔታ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት በሚያወጣው የግዥ ጨረታ ላይ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

ሀ/ የሙስና ተግባር ማለትም በግዥ ሙያ ላይ ለተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ ጉቦ ወይም ማባበያ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለውን ነገር መስጠቱ፣

ለ/ የማጭበርበር ማለትም ሀሰተኛ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ሰነድ ማቅረቡ ወይም በኤጀንሲው ታግዶ እያለ የእገዳው ጊዜ ሳይጠናቀቅ በሌላ ጨረታ ላይ ተካፍሎ መገኘቱ ወይም ከውል ውጭ ጥራት የጎደለውን ዕቃ ወይም አግልግሎት ወይም የግንባታ ስራ ወይም የምክር አገልግሎት ዕውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስመስሎ ማቅረቡ፣

ሐ/ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ተመሳጥሮ ዋጋ በመወሰን ሌሎች ተጫራቾችና መ/ቤቱ ከነጻ ውድድር ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም ማሳጣቱ፣

መ/ ከመንግስት መ/ቤት ሰራተኞች ወይም ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከውሉ ውጭ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ማቅረቡ፣

ሠ/ በግዥ ስራ ላይ የተሰማራን ባለሙያ ወይም ኃላፊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጉዳቱ ወይም ለመጉዳት ማስፈራራቱ (መዛቱ) ወይም ማስገደዱ፣

ረ/ ቀደም ሲል በኤጀንሲው የተጣለበትን ቅጣት ከፈጸመ ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ዓመት ውስጥ ሌላ እገዳ የሚያስከትል ጥፋት መፈጸሙ፣

፵፯.፳.፪ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

ሀ/ በገባው ውል መሠረት አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን፣ ባለማጠናቀቁ ወይም አቅርቦቱን ጀምሮ በማቋረጡ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ወይም የጥቅም ማጣት ካስከተለ፣

ለ/ በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ መሆኑ በጽሁፍ ተገልጾለት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት መ/ቤቱ ግዥውን ከሌላ ተጫራች በመፈጸሙ በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ካስከተለበት፣

ሐ/ ከዚህ ቀደም (ከ፫ ዓመት ወዲህ) ሌላ ጥፋት ፈጽሞ በኤጀንሲው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ አሁን የቀረበበት ሪፖርት ሌላ ማስጠ ንቀቂያ የሚያሰጥ የግዥ አፈጻጸም ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፣ እንደ ጥፋቱ ክብደት እየታየ ከስድስት ወር ላለነሰና ከሁለት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ጨረታ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

፵፯.፫.፫ ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሀ/ ውል ገብቶ አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በመ/ቤቱ ሥራ ላይ ችግር በመፍጠሩ፣

ለ/ መ/ቤቶች ግዥ ለመፈፀም በሚያወጡት የአካባቢ ማስታወቂያ ላይ አቅራቢው ሆን ብሎ ለመሳተፍ አለመፈለጉ ከተረጋገጠ፣

፵፯.፫.፬ ኤጀንሲው ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፵፮.፫.፩ እና ፵፮.፫.፪ መሠረት የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ለሁሉም የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች፣ በክልል ለሚገኙ ኮሌጆች፣ ተቋማት፣ ማዕከላት እና ለፌዴራል ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

፵፯.፫.፭ ኤጀንሲው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መ/ቤቶች ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ በግዥ ውላቸው እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

፵፯.፬ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፫ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ወይም አቅራቢ የጥፋተኝነት ሪፖርት ካቀረበው መ/ቤት ባገኘው አድራሻ የፁህፍ ማስታወቂያውን ለማድረስ ጥረት አድርጎ ካልተሳካለት ማስታወቂያውን ለአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት የጥፋተኝነት ሪፖርት ባቀረበው መ/ቤት ባስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ ላይ እንዲለጠፍ ካደረገ በኋላ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

፵፯.፭ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ ፬ ላይ በተገለፀው አግባብ ኤጀንሲው በወሰነው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ወይም አቅራቢ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 49 መሠረት ጉዳዩን አግባብነት ወዳለው ፍርድ ቤት

ከማቅረቡ በፊት የወሰነበትን ውሳኔ እንደገና እንዲያይለት ኤጀንሲውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ኤጀንሲውም ጥያቄውን ተቀብሎ በአግባቡ ከመረመረ በኋላ ቀደም ሲል የወሰነውን ውሳኔ ሊያሻሽል ወይም ሊያስቀር የሚችል አሳማኝ ምክንያት መቅረቡን ካረጋገጠ ቀደም ሲል የወሰነውን ውሳኔ በከፊል ሊያሻሽል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊያነሳ ይችላል፡፡

## ፵፰. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር

፵፰.፩ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ደርሷል የሚባለው አቅራቢው ድንገት ደራሽ በሆነ ሁኔታ የውል ግዴታውን እንዳይፈጽም ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ባጋጠመው ጊዜ ነው፣

፵፰.፪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላሉ፣

ሀ/ ውል እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣

ለ/ እንደ መሬት መናወጥ፣ መብረቅ፣ ማዕበል እና ይህን የመሳሰሉ ፍጥረታዊ አደጋዎች፣

ሐ/ የጠላት፣ የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣

መ/ ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣

ሠ/ በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች፣ ናቸው፡፡

፵፰.፫ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፡-

ሀ/ በተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት ባንደኛው መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ውስጥ የተደረገ የሠራተኛ አድማ ወይም የመ/ቤት መዘጋት፣

ለ/ ለውሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣

ሐ/ ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም ወጪ የሚያከብድበት የአዲስ ህግ መውጣት፣

## ፵፱. አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት

ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፺፬፣ ፺፮ እና ፺፯ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቱ፣ ቦርዱ ወይም ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ዕጩ ተወዳዳሪ፣ ተጫራች ወይም አቅራቢ ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ፲፫

## የተሻሩ መመሪያዎች እና ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ

### ፺. የተሻሩ መመሪያዎች፣

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ታህሳስ ፩ ፳፻፲፫ ዓ/ም የወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ እና ለከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም አፈፃፀም ተብሎ ከወጣው ሥርኩላር በስተቀር በተለያየ ጊዜ የወጡ ማሻሻያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

### ፺፩. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከታህሳስ ፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ታምራት ዲላ ኢያሱ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ

ሀዋሳ